# የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# የተማሪ ወላጆች ማህበር (የተወማ) አደረጃጀትና አተገባበር መመሪያ

ህዳር 2012 ዓ/ም

አዲስ አበባ

# የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ለተማሪ ወላጆች ማህበር አደረጃጀትና አተገባበር የወጣ መመሪያ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአጠቃላይ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲውን በከተማው በሚገኙ የመንግስት የግልና መንግስታዊ ባልሆኑ የትምህርት ተቋማት በመተግበር የትምህርት ጥራትንና ፍትሃዊነትን በማዳረስ በሀገሪቱ ሰላማዊ ዲሞክራሲያዊና መልካም አስተዳደርን ለመገንባት እንዲቻል ብቁ ዜጋ ለማፍራት እየሰራ ይገኛል፡፡ እነዚህን ኃላፊነቶች በብቃት ለመወጣት ትርጉም ያለው የህብረተሰብ ተሳትፎ ሲኖር እንደሚገባ ይታመናል፡፡ ህብረተሰቡ ለትምህርት ተቋማት ህልውና ካለው ጠቀሜታና ተጠቃሚነት አኳያ የመማር ማስተማሩን ስራ በባለቤትነት እንዲመራ ወጥ የሆነ አደረጃጀት መፍጠር በማስፈለጉ፤

የትምህርት  ተቋማትን ያሳካተተ በመሆኑ ህብረተሰቡን በትምህርት ቤት አመራር በወጥነትና በንቃት በሁሉም የትምህርት ተቋማት በተገቢው ደረጃ መሳተፍ ሳይቻል ቆይቷል፡፡ እንዲሁም መጋቢት 2010 ዓ/ም ተሻሽሎ የወጣዉም መመሪያ በግልና መንግስታዊ ባልሆኑ ትምህርት ቤቶች የሚታዩ  ችግሮችን በተደራጀ እና በተቀናጀ አግባብ ታግሎ የማስተካከል ሂደቱ አዝጋሚ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ በመሆኑም ህብረተሰቡ በሰፊው የሚሳተፍበትን ሥርዓት በመዘርጋት የፖሊሲው ተጠቃሚዎች እንዲሆኑ ለማስቻል በመማር ማስተማር ሂደቱ ላይ ተገቢ ውሣኔዎችን በማስተሳሳፍ በትምህርት ስርዓቱ ውስጥ ህብረተሰቡ ቀደም ሲል በየካቲት 2004 ዓ.ም የወጣው የወተመህ አደረጃጀትና አፈፃፀም መመሪያ የግልና መንግስታዊ ያልሆኑ የባለቤትነት ሚና እንዲጫወት ለማድረግ መጋቢት 2010 ዓ/ም የወጣውን መመሪያ ማሻሻል አስፈልጓል፡፡

ስለሆነም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ አዋጅ ቁጥር 35/2004 አንቀጽ 9 ንኡስ አንቀፅ 2 በተሰጠው ስልጣን መሰረት የአጠቃላይ ትምህርት ዘርፍ ሁሉም ተቋማት ወላጆችን በተገቢው አደረጃጀት ለማሳተፍ ይቻል ዘንድ ይህንን መመሪያ አሻሽሎ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌ

### አንቀፅ 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ በመንግስት፣ በግል እና መንግስታዊ ባልሆኑ ትምህርት ቤቶች የተማሪ ወላጅ ማህበር አደረጃጀትና አተገባበርን ለማቋቋም የወጣ መመሪያ ቁጥር 2012 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### አንቀፅ 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፤

ሀ. "ምክር ቤት" ምክር ቤት ማለት በወላጆች የሚሰየምበየደረጃዉ የሚቋቋም የአመራር አካል ነዉ፡፡

ለ. "ቢሮ" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ነው፡፡

ሐ."ባለስልጣን" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትምህርትና ስልጠና ጥራት፣ሙያ ብቃት ምዘናና ማረጋገጫ ባለስልጣን ማለት ነው፡፡

መ. "የግል ትምህርት ቤት" ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትምህርትና ስልጠና ጥራት፣ሙያ ብቃት ምዘናና ማረጋገጫ ባለስልጣን እውቅና የተሰጠውና በግል ባለሀብት ባለቤትነት የሚተዳደር ትምህርት ቤት ነው፡፡

ሠ. "መንግስታዊ ያልሆነ ትምህርት ቤት" ማለት የትምህርትና ስልጠና ጥራት፣ሙያ ብቃት ምዘናና ማረጋገጫ ባለስልጣን ዕውቅና ያለው በኮሚኒቲ ፣ በህዝብ፣ በሃይማኖት ተቋማት በድርጅት ባለቤትነት የሚተዳደር ኖኖ ዜጐች በእውቀትና በክህሎት የሚቀረፁበት የአመለካከት ለውጥ የሚያመጡበት ተቋም ነው፡፡

ረ. "መምህር" ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባሉት በመንግስት፣በህዝብ፣ በግል ወይም መንግስታዊ ባልሆኑ ት/ቤቶች በመምህርነት ሙያ ሰልጥኖ በመምህርነት ስራ ላይ የተሰማሩ ማለት ነዉ ፡፡

ሸ. "ጠቅላላ ጉባኤ" ማለት በትምህርት ቤቱ የሚማሩ የተማሪ ወላጆች ወይም አሳዳጊ የሚሳተፉበት ጠቅላላ ስብሰባ ነው፡፡

ቀ. "ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ" ማለት በወላጅ መምህራን ጠቅላላ ጉባኤ በዴሞክራሲያዊ መንገድ የሚመረጥና ተጠሪነቱ ለወላጅ መምህራን ጠቅላላ ጉባኤ የሆነ የአመራር አካል ነው፡፡

በ. "ክፍለ ከተማ ማለት" በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር ቁጥር 361/1995 ዓ.ም አንቀፅ 2.5 መሠረት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሁለተኛ ደረጃ የአስተዳደር እርከን ነው፡፡

ተ. "ወረዳ" ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር ቁጥር 361/1995 ዓ.ም አንቀፅ 2.5 መሠረት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሶስተኛ ደረጃ የአስተዳደር እርከን ነው፡፡

ቸ. "የተ.ወ.ማ/ወ.ተ.መ.ህ/ወ.መ.ሕ/"ማለት በመንግትስት በግል ወይም መንግስታዊ ባልሆነ ት/ቤቶች የተቋቋመ የወላጅ የተማሪና የመምህር ሕብረት ማለት ነው፡፡

ጎ. "ተማሪ" ማለት በትምህርት ቤቶችም ሆነ በመምህራን ስልጠና ኮሌጆች በመደበኛ ወይም መደበኛ ባልሆነ ትምህርት ስመማር ተመዝግቦ በትምህርት ተቋሙ ደንብና መመሪያ መሰረት ትምህርቱን በመከታተል ላይ ያለ ግለሰብ ነው፡፡

## አንቀጽ 3 የፆታ አገላለፅ

በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገፀው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

## አንቀጽ 4 የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ሥር በሚገኙ በአሥሩ ክ/ከተሞች እና ወረዳዎች ያሉ የመንግስት ፣ የግልና መንግስታዊ ያልሆኑ ፣ የሕዝብ እና ቅድመ መጀመሪያ የመጀመሪያ ደረጃ እና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## አንቀፅ 5 የመመሪያው ዓላማ

ሀ. በየትምህርት ቤቱ ወላጆች በመማር ማስተማር ሂደቱ በትምህርት ቤት ዕቅድና ዝግጅት፣በግብዓት አቅርቦትና ምቹ ትምህርት ቤት አካባቢና ሁኔታ (ስመማር ማስተማር) መሳተፋቸው እና የድርሻቸውን እንዲወጡ ማስቻል፣

ለ. በወላጆች ፣በተማሪዎች ፣በመምሀራንና በትምህርት ቤቱ አመራር መካከል ጠንካራና ጤናማ ግንኙነቶች መፍጠርና ውጤታማ የትምህርት አገልግሎት በመስጠት የትምህርት ጥራትን ስማረጋገጥ ነው፡፡

ሐ. ወላጆች ትምህርት ቤቶችን በባለቤትነት በተጠያቂነትና በተቆርቋሪነት እዲመሩ ማስቻል፣ በትምህርት ቤቶችና በወላጆች መካከል ጠንካራ ድልድይ ሆኖ ማገልገል ።

## አንቀፅ 6. ይህ መመሪያ በሚከተሉት የሕብረተሰብ ተሣትፎ መርሆዎች መሰረት ተግባራዊ ይሆናል

6.1. **ተባባሪነት፡** ሕጻናት እና ወላጆችን ለማገልገል ከሁሉም አጋሮችጋርበጋራ መሥራት ።
6.2. **ዝግጁነት፡** በወላጆች እና በማህበረሰብ ተሳትፎ ለሕጻናት ትምህርት ስኬት ጤናና ማህበራዊ ህልውናን ለመጠበቅ በቁርጠኝነት መሥራት።
6.3. **ብዝሐነት፡** የሁሉንም እምቅ አቅም ያለ ልዩነት ዕድሜ ጾታ ባህል ኢኮኖሚያዊ ደረጃ ትምህርት ደረጃ ዘር ሃይማኖት ህጋዊ ሰውነት ጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ ጋብቻ ሁኔታ የወላጅ ደረጃ እውቅና መስጠት።
6.4. **አካታችነት፡** የአካል ጉዳተኞችንና የልዩ ፍላጎት ትምህርት ያላቸውን ሕጻናት ተማሪዎች ተሳትፎ ማሳደግ።
6.5. **ቅንነት፡** የሁሉንም የህብረቱን አባላት ሠራተኞች በጎ ፍቃደኞች አጋሮች ተሳትፎ ዋጋ መስጠት ።
6.6. **ተጠያቂነት፡** ለማህበሩ ስትራቴጂያዊ ተነሳሽነት ሁሉም የማህበሩ አካላት የጋራ ኃላፊነት መውሰድ ።

## ክፍል 2

### ምዕራፍ 7 . የተ.ወ.ማ/የወተመህ/ወመሕ አወቃቀርና አደረጃጀት

### ክፍል 7.1 አወቃቀር

#### 7.1.1. የአገር አቀፍ የተማሪ ወላጆች ማህበር አወቃቀር

አገር አቀፍ የተማሪ ወላጆች ማህበር ሁሉንም ክልል ከተማ አስተዳደር በሚወከሉ አምስት አምስት አባላት ይወክላል፣ህብረቱም ሁለት አካላት ይኖሩታል ፣ እነዚህም ምክር ቤቱ እና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ይሆናሉ ።

#### 7.1.2. የአገር አቀፍ የተማሪ ወላጆች ማህበር የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አደረጃጀት

በአገር አቀፍ ደረጃ የሚቋቋመው የተማሪ ወላጆች ማህበር ጠቅላላ ጉባዔ ከየ ክልሉ ወይም ከተማ አስተዳደር የተወከሉ አምስት አምስት አባላት ማለትም በጠቅላላው 55 የምክር ቤት አባላት ይኖሩታል።

#### 7.1.3. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተማሪ ወላጆች ማህበር የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አደረጃጀት

ከምክር ቤት አባላት መካከል በሚመረጥ አስመራጭ ኮሚቴ አማካነት ከየክልሉ ወይም ከተማ አስተዳደሩ የሚመረጡ አንድ አንድ ተወካዮች የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ይሆናሉ፣፣ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ እና ጾታን ባገናዘበ መልኩ የሚመረጡ 11 አባላት ይኖረዋል።

#### 7.1.4. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተማሪ ወላጆች ማህበር ምክር ቤት አደረጃጀት

የአዲስ አበባ ከተማ አሰተዳደር የተማሪ ወላጆች ማህበር ምክር ቤት ከክፍለ ከተማ በሚወከሉ አስር አስር የክፍለ ከተማ ስራ አስፈጻሚ ይመሰረታል። የከተማ አስተዳደር የወላጆች ማህበር ሥራ አስፈጻሚ ከእያንዳዱን ክፍለ ከተማ አንድ አንድ አባላት በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ እንዲያገለግሉ ይሰይማል። የከተማ አስተዳደሩ የተማሪ ወላጅ ማህበር ሥራ አሰፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ብዛት በከተማ አስተዳደር በሚገኙ ክፍለ ከተማ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴዎች ጠቅላላ 110 ሲሆኑ የከተማ አስተዳደሩ የተ.ወ.ማ. ፕሬዝደንት 1 በድምሩ 111 የምክርቤት አባላት ይኖሩታል። በስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ፕሬዝዳንት፣ ምክትል ፕሬዝዳንት፣ጸሐፊ፣ሒሳብ ሹም፣ኦዲተር እና ገንዘብ ያዥ የሚመረጡት ከመንግስት የትምህርት ተቋማት ብቻ ይሆናል።ከስራ አስፈጻሚ 3ቱ ከግል ትምህርት ቤት የተወከሉ ይሆናሉ።

#### 7.1.5. የክፍለ ከተማ የተማሪ ወላጆች ማህበር ምክር ቤት አደረጃጀት

የክፍለ ከተማ የተማሪ ወላጆች ማህበር ምክር ቤት በስራቸው ካሉ ወረዳዎች ብዛት ወይም ተጨባጭ የትምህርት ቤት ብዛት የሚከፋፈል 150 የሚሆን ድምጽ የሚሰጡ የተማሪ ወላጅ ሕብረት ይሳተፋሉ። የክፍለ ከተማ የተማሪ ወላጆች ማህበር ሥራ አስፈጻሚ በምክርቤት የሚወከሉ 11 ስራ አስፈጻሚ ይኖሩታል ። በስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሊቀመንበር ፣ ምክትል ሊቀመንበር ፣ ጸሐፊ ፣ ሒሳብ ሹም ፣ ኦዲተር እና ገንዘብ ያዥ የሚመረጡት ከመንግስት የትምህርት ተቋማት ብቻ ይሆናል። ከስራ አስፈጻሚ 3ቱ ከግል ትምህርት ቤት የተወከሉ ይሆናሉ።

#### 7.1.6. የወረዳ የተማሪ ወላጆች ማህበር ምክር ቤት አደረጃጀት

የወረዳ የተማሪ ወላጆች ማህበር ምክር ቤት ከየትምህርት ቤቱ ተመርጠው በሚመጡ አራት አራት ወላጅ አመራሮች ይመሰረታል። ምክር ቤቱ ቁጥራቸው ከ5 እስከ 7 የሚደርሱ አባላት በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው እንዲያገለግሉ ይሰየማሉ። በስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሊቀመንበር ፣ ምክትል ሊቀመንበር ፣ጸሐፊ፣ሒሳብ ሹም ፣ ኦዲተር እና ገንዘብ ያዥ የሚመረጡት ከመንግስት የትምህርት ተቋማት ብቻ ይሆናል። ሆኖም የትምህርት ቤት ወ.መ.ሕ ወይም ወተመሕ የምክርቤት አባላት ቁጥር እስከ ሰላሳ ይሆናል ።

### 7.1.7. የትምህርት ቤት የወላጆች ተማሪ መምህር ህብረት አደረጃጀት

የትምህርት ቤት የወላጆች ተማሪ መምህር ህብረት ሁለት አካላት ይኖሩታል ። እነዚህም የትምህርት ቤት የወላጆች ተማሪ መምህር ህብረት ጠቅላላ ጉባኤ እና ምክር ቤት ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ናቸው ። የትምህርት ቤት የወላጆች ተማሪ መምህር ህብረት ጠቅላላ ጉባኤ ሁሉንም የትምህርት ቤቱን ተማሪ ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች የሚያቅፍ ሆኖ ቁጥራቸው ከ9 እስከ 11 የሚደርሱ የሥራ አስፈጻሚ አካላት ይሰይማል ። ጠቅላላ ጉባኤው በስሩ የተለያዩ ተግባራትን የሚያከናውኑ ኮሚቴዎችን ያደራጃል ። በተጨማሪም እንደ ትምህርትቤቶቹ ነባራዊ ሁኔታ የሚከተሉት ዝርዝር አሰራሮች ይኖሩታል፡-

7.1.7.1. **በየክፍሉ የተደራጁ የወተመህ ኮሚቴ አባላት** የትምህርት ቤቱ የተማሪዎች ወላጆች የሚሳተፉበት ጠቅላላ ስብሰባ የምክር ቤቱ አባል ይሆናል፡፡ ሆኖም አንዳንድ የግልና መንግስታዊ ያልሆኑ ትምህርት ቤቶች ሁለትና ከዚያ በላይ የማስተማሪያ ተቋማት (ቁጥር 1፣2፣3..) ወይም ቅርንጫፍ ያላቸው የተቋማቱ ብዛት የወላጆች ጠቅላላ ጉባኤ ይወስናል፡፡

7.1.7.2. **ለትምህርት ቤት የወተመህ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አደረጃጀት በተመለከተ** በወላጆችና መምህራን ጠቅላላ ጉባኤ የሚመረጥ /የሚሰየም/ እንደ ትምህርት ቤቱ ስፋትና ጥበት ነባራዊ ሁኔታውን ያገናዘበ ዝቅተኛው ስድስት ወላጅ ሦስት መምህር እና ሁለት ተማሪ አስራ አንድ አባላት የያዘ የአመራር አካል ይኖረዋል፡፡

7.1.7.3. **የተለያዩ ትምህርት ቤት ያላቸው የግልና መንግስታዊ ያልሆኑ ትምህርት ቤቶች ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አደረጃጀት** ከሁለት በላይ ትምህርት ቤቶች ያላቸው የግልና መንግስታዊ ያልሆኑ ትምህርት ቤቶች ከእያንዳንዱ ተቋም የየራሳቸውን አምስት አባላት ያሉ ወተመህ ኮሚቴ ይመርጣሉ፡፡ እነዚህ የየቅርንጫፉ (ካምፓስ) የወተመህ ኮሚቴ አባላት በጋራ ሆነው የአጠቃላይ የት/ተቋማቱ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ይሆናሉ፡፡

7.1.7.4. የስራ አስፈፃሚው አሰያየም ሰብሳቢ፣ም/ሰብሳቢ ፀሐፊ፣ ገንዘብ ያዥ ፣ሒሳብ ሹምና ኦዲተር ይኖሩታል፡፡

7.1.7.5. የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር እንደ አስረጅ ሆኖ ተሳታፊ ይሆናል፣ አጀንዳዎች ያቀርባልእንዲሁም

ኮሚቴው የሚፈልገው መረጃም ይሰጣል፡፡

7.1.7.6. የምክር ቤቱ የስራ ዘመን ሦስት ዓመት ይሆናል፡፡ በድጋሚ ከተመረጡ ሊሰሩ የሚችሉት ለአንድ የምርጫ ዘመን ብቻ ሊሰራ ይችላል፣

7.1.7.7. የመንግስት የግልና መንግስታዊ ያልሆነ የትምህርት ተቋም ወተመህ እንዲቋቋም ለማድረግ ተቋሙ የሚገኝበት ክ/ከተማ ወይም ወረዳ ት/ጽ/ቤት ኃላፊ ወይም ተወካይ ባሉበት የትምህርት ቤቱ የወላጅና መምህራን ምልአተ ጉባኤ መኖሩ ከተረጋገጠ በኋላ ኃላፊው ወይም ተወካዩ አላማውን አስረድቶ ከተማመኑ በኋላ በዴሞክራሲያዊ መንገድ ከሶስት እስከ አምስት (3-5) የሚሆኑ ከተማሪ ወላጆች የተውጣጡ አስመራጭ ኮሚቴዎች ይሰይማል፡፡

7.1.7.8. አስመራጭ ኮሚቴውም መድረኩን ተረክቦ የምርጫውን ሂደት በባለቤትነት ይመራል፡፡ በምርጫ ህግ መሰረት ምርጫውን አጠናቆ ለምልአተ ጉባኤው አሳውቆና በቃለ-ጉባኤ ተፈራርሞ ኮሚቴውን በማቋቋም ኃላፊነቱን ለኮሚቴው በማስረከብ ስራውን ያጠናቅቃል፡፡

7.1.7.9. አስመራጭ ኮሚቴው ምርጫው የሁለቱም ጾታ ተዋጽኦ ያማከለ እንዲሆን ግንዛቤ ይፈጥራል፤ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

7.1.7.10. የተቋቋመው የትምህርት ቤት ወተመህ ከርዕሰ መምህሩን ጋር በመሆን የክፍል ወተመህ ያቋቁማል፣

## 7.2. የመንግስት፣የግልና መንግስታዊ ያልሆኑ የትምህርት ተቋማት የወላጅ ተማሪና መምህር ጠቅላላ ጉባኤ ተግባርና ኃላፊነት

7.2.1. የትምህርት ቤቱ ውሳኔ ሰጭ አካል ይሆናል

7.2.2. በሥራ አስፈፀሚ ኮሚቴ ተዘጋጅቶ የሚቀርበውን እቅድ ይመረምራል፣ ያፀድቃል

7.2.3. ችግሮች ሲፈጠሩ የትምህርቱን አጠቃላይ ሁኔታ በቅርበት የሚከታተልና የሚያጣራ ጊዜያዊ ኮሚቴ ይሰይማል

7.2.4. የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሪፖርት ይመረምራል ፣ ያፀድቃል

7.2.5. በዓመት ሁለት ጊዜ የወላጆች ጠቅላላ ጉባዔ ያካሂዳል።

## 7.3. የከተማ አስተዳደር የተማሪ ወላጆች ማህበር ምክር ቤት ተግባር እናኃላፊነት

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተማሪ ወላጆች ማህበር ምክር ቤት ከክፍለ ከተማ በሚወከሉ አስር አስር የክፍለ ከተማ ስራ አስፈጻሚ ይመሰረታል። የከተማ አስተዳደር የወላጆች ማህበር ሥራ አስፈጻሚ ከእያንዳንዱ ክፍለ ከተማ አንድ አንድ አባላት በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ እንዲያገለግሉ ይሰይማል። የከተማ አስተዳደሩ ሥራ አሰፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ብዛት በከተማ አስተዳደር በሚገኙ ክፍለ ከተማ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴዎች ጠቅላላ 100 ሲሆኑ የከተማ አስተዳደሩ የተ.ወ.ማ. ፕሬዝደንት 1 በድምሩ 100 የምክርቤት አባላት ኖሮት ተግባርና ኃላፊነቱ እንደሚከተለው ይቀርባል፡-

7.3.1. የወላጅ ማህበር ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላትን ይሰይማል

7.3.2. የዓመቱን ዕቅድ ይገመግማል ያጸድቃል።

7.3.3. የዕቅድ አፈጻጸሙን ይገመግማል ግብረ መልስ ይሰጣል ።

7.3.4. ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው በለዩአቸው ችግሮች ላይ መፍትሄይሰጣል።

7.3.5. የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ከወከላቸው አባላት መካከል አመኔታ ያጣባቸውን ገምግሞ ይሽራል፣ በአዲሶችም ይተካል።

## 7.4. የከተማ አስተዳደር የተማሪ ወላጆች ማኀበር ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ኃላፊነትና ተግባር

የሥራ አስፈጻሚ ከሚቴው ተጠሪነቱ ለምክር ቤቱ ሆኖ የክፍለ ከተማ ሥራ አስፈጻሚ 11 አባላት ይኖሩታል ። ከሥራ አስፈጻሚው ውስጥ ፕሬዝዳንት ምክትል ፕሬዝዳንት ጸሐፊ ፣ገንዘብ ያዥ፣ሂሳብ ሹምና ኦዲተር እንዲሁም ሌሎች የንዑሳን ኮሚቴ ተጠሪዎች በአባላት ተመርጠው ይሰየማሉ። ሥራ አስፈጻሚው በወል የሚከተሉት ኃላፊነቶችና ተግባራት ይኖሩታል ።

1. በከተማ ደረጃ የሚከናወኑ የተማሪ ወላጅ ማህበር ተግባራትን ያቅዳል በምክር ቤቱ ያጸድቃል
2. የንዑሳን ኮሚቴዎችን ዕቅድ አፈጻጸም ይከታተላል ይደግፋል
3. በክልሉ የተቋቋመ ወላጆች ማህበር ዕቅድ አፈጻጸም ይከታተላልይደግፋል
4. የላቀ አፈጻጸም ላሳዩ በከተማ ለተቋቋሙ ተማሪ ወላጆች ማህበር ማበረታቻና ዕውቅና ይሰጣል፣የልምድ ልውውጥም ያዘጋጃል
5. በከተማ ውስጥ በየእርከኑ በተቋቋሙ የተማሪ ወላጆች ማህበር የተከናወኑ ተግባራትን ብተመለከተ የተለያዩ መገናኛ ብዙሃንን በመጠቀም የህብረተሰቡን ግንዛቤ ለማሳደግ መድረኮችን ያዘጋጃል
6. ከሚመለከታቸው የመንግሥት አካላትና ከልማት አጋሮች ጋር በመተባበር በትምህርት ሥራ የህብረተሰቡ ተሳትፎ የሚጎለብትበትን ዘዴ ይመክራል፣ያቅዳል፣ተግባራዊነቱንም ይከታተላል
7. በየሩብ ዓመቱ ስብሰባ ያካሂዳል ።

### 7.4.1. የፕሬዚዳንት ተግባርና ኃላፊነት

1. ማህበሩን ወክሎ በተለያዩ ክልል አቀፍ ስብሰባዎች ላይ ይገኛል
2. የተማሪ ወላጆች ማህበርን ስትራቴጂያዊ ዓላማዎች ይለያል ፣ ነባራዊ ሁኔታን ያገናዘበ ዕቅድ ያዘጋጃል
3. የተማሪ ወላጆች ማህበርን ተልዕኮና ዓለማ ማሳካት የሚያስችል የወላጆችንየሥራ ፕሮግራሞችና ፕሮጄክቶችን ይነድፋል ሀብት ያፈላልጋል

4. የተማሪ ወላጆች ምክር ቤትና የሥራ አስፈጻሚውን ኮሚቴ ስብሰባ ይጠራል ይመራል
5. መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑድርጅቶች ጋር በቅንጅት ይሠራል
6. የተማሪ ወላጆች ሥራዎችን ያስተባብራል
7. ወላጆችን ከማህበረሰቡና ከሴክተር መሥሪያ ቤቶች በማገናኝ ኃላፊነቱን ይወጣል
8. ከምክትል ፕሬዝዳንቱ እና ከሂሳብ ሹሙ ጋር በጋራ በመሆን ፋይናንስን ይመራል
9. ማህበሩን ወክሎ ይከሳል ይከሰሳል

### 7.4.2. የምክትል ፕሬዝዳንት ተግባርና ኃላፊነት

1. ፕሬዝዳንቱ በማይገኝበት ወቅት እሱን ተክቶ የሠራል
2. የተማሪ ወላጆች ማህበርን ስትራቴጂያዊ ዓላማዎች ይለያል
3. ነባራዊ ሁኔታን ያገናዘበ ዕቅድ ከፕሬዚዳንቱ ጋር በመመካከር ያዘጋጃል
4. የተማሪ ወላጆችን ተልዕኮና ዓላማ መሳካት የሚያስችል የወላጆችን የሥራ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶችን ይነድፋል ሀብት ያፈለልጋለ
5. የተማሪ ወላጆች ምክር ቤትና የሥራ አስፈጻሚውን ኮሚቴ ፕሬዝዳንቱ በሌለበት በሰብሳቢነት ይመራል፣
6. መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑድርጅቶች ጋር በቅንጅት ይሠራል
7. የተማሪ ወላጆች ሥራዎችን ያስተባብራል
8. ወላጆችን ከማህበረሰብና ከሴክተር መሥሪያ ቤቶች በማገናኘት ኃላፍነቱን ይወጣል
9. ከፕሬዝዳንቱ እና ከሂሳብ ሹሙ ጋር በጋራ በመሆን ፋይናንስን ይመራል

### 7.4.3. የጸሐፊ ተግባርና ኃላፍነት

1. የተማሪ ወላጅ ማህበር ስብሰባ አጀንዳዎችን ከፕሬዚደንቱ ጋር በመመካከር አዘጋጅቶ ያቀርባል
2. የተማሪ ወላጆች ማህበር ስብሰባ ቃለጉባኤ ይይዛል
3. የስብሰባውን ቃለጉባኤ በመመዝገብ አባላት ከሚቀጥለው ስብስባ በፊት እንዲያውቁት ያደርጋል
4. ሌሎች የጥሪና በደብዳቤ የሚደረጉ ግንኙነቶችን በማዘጋጀት ያሰራጫል
5. የማህበሩን የጽሁፍ መዛግብትና ሌሎች መረጃዎችን በማደራጀት ይይዛል
6. የማህበሩን ማህተም ይይዛል

### 7.4.4. የሂሳብ ሹም ተግባርና ኃላፍነት

1. የሂሳብ መረጃዎችን በመሰብሰብ ይተነትናል፣ሂሳብ በተያዘ የጊዜ ገደብ ይዘጋል
2. የወጪ ጥያቄዎች ሲቀርቡ ትክክልነታቸውን በማረጋገጥ ባግባቡ ያስተናግዳል
3. የሂሳብ መዛግብቶችን ያደራጃል
4. የሂሳብ ምርመራ ጥያቄ ሲቀርብ ሰነዶችን ያስመረምራል
5. ባመታዊ የዕቅድና በጀት ዝግጅት ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል
6. በበጀት አጠቃቀም ምክር ይሰጣል

### 7.4.5. የኦዲተር ተግባር እና ኃላፊነት

1. የሂሳብ ምርመራ ወይም ኦዲቲንግ ዕቅድ ያዘጋጃል ፣
2. የወጪ ትዛዞች በተያዘ የበጀት ዕቅድ መሆኑን ያረጋግጣል
3. የሂስብ መዝገቦች በትክክል መያዛቸውን ያረጋግጣል ፣
4. የሂሳብ ስነዶችን በተያዘ ዕቅድ መሠረት ይመረምራል ፣
5. የሂሳብ ሪፓርቶችን በማዘጋጀት ለምክር ቤቱ በየግማሽ ዓመቱ ያቀርባል፣
6. በሂሳብ አያያዝ ወይም አሰራር ምክር ለሚመለከተው ይሰጣል

### 7.4.6. የገንዘብ ያዥ ተግባርና ኃላፊነት

1. የማህበሩ ገንዘብ ያዥ ተጠሪነቱ ለሥራ አስፈጻሚው ሆኖ የሚመረጠውወላጅ ኃላፊነት የሚሰማውና ተአማኒ መሆን ይኖረበታል
2. የወላጆች ሀብረት ሂሳብ ይይዛል ፣ስለ ገንዘቡም ሪፖረት ያደርጋል
3. ትክክለኛ የወጪና የገቢ የሂሳብ ሰነዶችን መዝግቦ ይይዛል
4. በሚመለከተው አካል በታዘዘ ጊዜ የወጪና ገቢ ክፍያዎችን ይፈጽማል
5. ገቢ ሂሳቦችን በዕለቱ በባንክ ገቢ ያደርጋል ፣ ወርሃዊ የባንክ የሂሳብሪፖርቶችን መዝግቦ ይይዛል
6. ሂሳቡን በተፈለገ ጊዜ ኦዲት ያስደርጋል

### 7.5. የክፍለ ከተማ የተጠማ ምክር ቤት ተግባርና ኃላፊነት

1. የክፍለ ከተማው የተጠማ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ያቀረበውን ዕቅድ ይመረምራል ያፀድቃል
2. የተጠማ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ያከናወናቸውን ተግባራት ሪፖርት ያዳምጣል ገምግሞ ያፀድቃል
3. በስሩ ከሚገኙ ምክር ቤቶች ጋር የጋራ መድረክ በማዘጋጀት መከታተል የተኩረት አቅጣጫዎችን ያስቀምጣል፣
4. ተጠሪነቱ ለከተማው የተጠማ ምክር ቤት ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል

### 7.6. የክፍለ ከተማ የተማሪ ወላጆች ማኅበር ሥራአስፈጻሚ ኮሚቴ ኃላፊነትና ተግባር

የሥራ አስፈጻሚ ከሚቴው ተጠሪነቱ ለምክር ቤቱ ሆኖ የክፍለ ከተማ ሥራ አስፈጻሚ 11 አባላት ይኖሩታል ። ከሥራ አስፈጻሚው ውስጥ ሊቀመንበር፣ ምክትል ሊቀመንበር ጸሐፊ

ገንዘብ ያዥ፣ሂሳብ ሹምና ኦዲተር እንዲሁም ሌሎች የንዑሳን ኮሚቴ ተጠሪዎች በአባላት ተመርጠው ይሰየማሉ። ሥራ አስፈጻሚው በወል የሚከተሉት ኃላፊነቶችና ተግባራት ይኖሩታል

1. በክፍለ ከተማ ደረጃ የሚከናወኑ የተማሪ የወላጅ ማህበር ተግባራትን ያቅዳል በምክር ቤቱ ያጸድቃል

2. የንዑሳን ኮሚቴዎችን ዕቅድ አፈጻጸም ይከታተላል ይደግፋል

3. በክፍለ ከተማዉ የተቋቋመ የተማሪ ወላጆች ማህበር ዕቅድ አፈጻጸም ይከታተላልይደግፋል

4. የላቀ አፈጻጸም ላሳዩ በክፍለ ከተማ ለተቋቋሙ የተማሪ የወላጅ ማህበር ማበረታቻና ዕውቅና ይሰጣል፣የልምድ ልውውጥም ያዘጋጃል

5. በክፍለ ከተማዉ ውስጥ በየርከኑ ብተቋቋሙ የተማሪ ወላጆች ማህበር የተከናወኑተግባራትን በተመለከተ የተለያዩ መገናኛ ብዙሃንን በመጠቀም የህብረተሰቡን ግንዛቤ ለማሳደግ መድረኮችን ያዘጋጃል

6. ከሚመለከታቸው የመንግሥት አካላትና ከልማት አጋሮች ጋር በመተባበር በትምህርት ሥራ የህብረተሰቡ ተሳትፎ የሚጎለብትበትን ዘዴ ይመክራል፣ያቅዳል፣ተግባራዊነቱንም ይከታተላል

7. በየሩብ ዓመቱ ስብሰባ ያካሂዳል

### 7.6.1. የሊቀመንበር ተግባርና ኃላፊነት

1. ማህበሩን ወክሎ በተለያዩ ክልል አቀፍ ስብሰባዎች ላይ ይገኛል
2. የተማሪ የወላጅ ማህበርን ስትራቴጂያዊ ዓላማዎች ይለያል ፣ ነባራዊ ሁኔታን ያገናዘበ ዕቅድ ያዘጋጃል
3. የተማሪ የወላጅ ማህበርን ተልዕኮና ዓለማ ማሳካት የሚያስችል የወላጆችንየሥራ ፕሮግራሞችና ፕሮጄክቶችን ይነድፋል ሀብት ያፈላልጋል
4. የተማሪ የወላጅ ማህበር ምክር ቤትና የሥራ አስፈጻሚውን ኮሚቴ ስብሰባ ይጠራል ይመራል
5. መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑድርጅቶች ጋር በቅንጅት ይሠራል
6. የተማሪ የወላጅ ማህበር ሥራዎችን ያስተባብራል
7. ወላጆችን ከማህበረሰቡና ከሴክተር መሥሪያ ቤቶች በማገናኘ ኃላፊነቱን ይወጣል
8. ከምክትል ሊቀመንበሩ እና ከሂሳብ ሹም ጋር በጋራ በመሆን ፋይናንስን ይመራል
9. ማህበሩን ወክሎ ይከሳል ይከሰሳል

### 7.6.2. የምክትል ሊቀመንበር ተግባርና ኃላፊነት

1. ሊቀመንበሩ በማይገኝበት ወቅት እሱን ተክቶ ይሠራል
2. የተማሪ የወላጅ ማህበርን ስትራቴጂያዊ ዓላማዎች ይለያል
3. ነባራዊ ሁኔታን ያገናዘን ዕቅድ ከሊቀመንበሩ ጋር በመመካከር ያዘጋጃል
4. የተማሪ የወላጅ ማህበርን ተልዕኮና ዓላማ መሳካት የሚያስችል የወላጆችን የሥራ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶችን ይነድፋል ሀብት ያፈለልጋለ
5. የተማሪ የወላጅ ማህበር ምክር ቤትና የሥራ አስፈጻሚውን ኮሚቴ ሊቀመንበሩ በሌለበት በሰብሳቢነት ይመራል
6. መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑድርጅቶች ጋር በቅንጅት ይሠራል
7. የተማሪ የወላጅ ማህበር ሥራዎችን ያስተባብራል
8. ወላጆችን ከማህበረሰብና ከሴክተር መሥሪያ ቤቶች በማገናኘት ኃላፍነቱን ይወጣል
9. ከሊቀመንበሩ እና ከሂሳብ ሹሙ ጋር በጋራ በመሆን ፋይናንስን ይመራል

### 7.6.3. የጸሐፊ ተግባርና ኃላፍነት

1. የተማሪ የወላጅ ማህበር ስብሰባ አጀንዳዎችን ከሊቀመንበሩ ጋር በመመካከር አዘጋጅቶ ያቀርባል
2. የተማሪ የወላጅ ማህበር ስብሰባ ቃለጉባኤ ይይዛል
3. የስብሰባውን ቃለጉባኤ በመመዝገብ አባላት ከሚቀጥለው ስብስባ በፊት እንዲያውቁት ያደርጋል
4. ሌሎች የጥሪና በደብዳቤ የሚደረጉ ግንኙነቶችን በማዘጋጀት ያሰራጫል
5. የማህበሩን የጽሁፍ መዛግብትና ሌሎች መረጃዎችን በማደራጀት ይይዛል
6. የማህበሩን ማህተም ይይዛል።

### 7.6.4. የሂሳብ ሹም ኃላፊነትና ተግባር

1. የሂሳብ መረጃዎችን በመሰብሰብ ይተነትናል፣ሂሳብ በተያዘ የጊዜ ገደብ ይዘጋል
2. የወጪ ጥያቄዎች ሲቀርቡ ትክክልነታቸውን በማረጋገጥ ባግባቡ ያስተናግዳል
3. የሂሳብ መዛግብቶችን ያደራጃል
4. የሂሳብ ምርመራ ጥያቄ ሲቀርብ ሰነዶችን ያስመረምራል
5. ባመታዊ የዕቅድና በጀት ዝግጅት ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል

6. በበጀት አጠቃቀም ምክር ይሰጣል

### 7.6.5. የኦዲተር ኃላፊነትና ተግባር

1. የሂሳብ ምርመራ ወይም ኦዲቲንግ ዕቅድ ያዘጋጃል
2. የወጪ ትዛዞች በተያዘ የበጀት ዕቅድ መሆኑን ያረጋግጣል
3. የሂስብ መዝገቦች በትክክል መያዛቸውን ያረጋግጣል
4. የሂሳብ ስነዶችን በተያዘ ዕቅድ መሠረት ይመረምራል
5. የሂሳብ ሪፖርቶችን በማዘጋጀት ለምክር ቤቱ በየግማሽ ዓመቱ ያቀርባል
6. በሂሳብ አያያዝ ወይም አሰራር ምክር ለሚመለከተው ይሰጣል

### 7.6.6. የገንዘብ ያዥ ተግባርና ኃላፊነት

1. የማህበሩ ገንዘብ ያዥ ተጠሪነቱ ለሥራ አስፈጻሚው ሆኖ የሚመረጠውወላጅ ኃላፊነት የሚሰማውና ተአማኒ መሆን ይኖረበታል
2. የወላጆች ህብረት ሂሳብ ይይዛል ፣ስለ ገንዘቡም ሪፖረት ያደርጋል
3. ትክክለኛ የወጪና የገቢ የሂሳብ ሰነዶችን መዝግቦ ይይዛል
4. በሚመለከተው አካል በታዘዘ ጊዜ የወጪና ገቢ ክፍያዎችን ይፈጽማል
5. ገቢ ሂሳቦችን በዕለቱ በባንክ ገቢ ያደርጋል ፣ ወርሃዊ የባንክ የሂሳብሪፖርቶችን መዝግቦ ይይዛል
6. ሂሳቡን በተፈለገ ጊዜ ኦዲት ያስደርጋል

## 7.7. የወረዳ የተማሪ ወላጆች ማህበር ምክር ቤት ተግባር እና ኃላፊነት

1. የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላትን ይሰይማል

2. የዓመቱን ዕቅድ ይገመግማል ያጸድቃል

3. ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው በለዩዋቸው ችግሮች ላይ መፍትሄ መስጠት

4. በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ከወከላቸው አባላት መካከል አመኔታ ያጣባቸውን መሻር

በአዲሶቹም መተካት

## 7.8. የወረዳ የተማሪ ወላጅ ማህበር ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ተግባር እና ኃላፊነት

የወረዳ የተማሪ ወላጅ ማህበር የሥራ ስፈጻሚ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለወረዳው ተማሪ ወላጆች ምክር ቤት ሆኖ ከ5 እስከ 7 አባላት ይኖሩታል ። ኮሚቴው ሊቀመንበር ፣ም፣ሊቀመንበር ጸሐፊ ሂሳብ ሹም ገንዘብ ያዥና ኦዲተር ሲኖሩት የሚከተሉት ኃላፊነቶችና ተግባራት በወል ይኖሩታል

1. የወረዳውን የተማሪ ወላጆች ማህበር ተግባራትን ያቅዳል ለምክር ቤት አቅርቦ ያጸድቃል

2. የንዑሳን ኮሚቴዎችን ዕቅድ አፈጻጸም ይከታተላል ይደግፋል

3. በመንግሥትና በግል ትምህርት ቤቶች የተቋቋሙ የወላጆች ተማሪ መምህራን ህብረት ወይም ወመህ ዕቅድ አፈጻጸም ይከታተላል ይደግፋል

4. የላቀ አፈጻጸም ላሳዩ በወረዳው ለተቋቋሙ የትምህርት ቤቶች የወላጆች ተማሪ መምህራን ህብረት ፣ወመህ ማበረታቻና እውቅና ይሰጣል ፣ የልምድ ልውውጥም ያዘጋጃል

5. በየትምህርት ቤቱ በተቋቋሙ የወላጆች ተማሪ መምህራን ህብረት ወይም ወመህ የተከናወኑ ተግባራትን በተመለከተ የተለያዩ መገናኛ ብዙሀንን በመጠቀም የህብረተሰቡን ግንዛቤ ለማሳደግ መድረኮችን ያዘጋጃል

6. ከሚመለከታቸው የመንግሥት አካላትና ከልማት አጋሮች ጋር በመተባበር በትምህርት ሥራ

የህብረተሰቡ ተሳትፎ የሚጎለብትበትን ዘዴ ይመክራል ፣ ያቅዳል ፣ተግባራዊነቱንም ይከታተላል

7.ከወረዳው የትምህርትና ስልጠና አመራር ቦርድ ጋር ጥብቅ ቁርኝት በመፍጠር የትምህርት ሥራን ይከታተላል

### 7.8.1. የሊቀመንበር ተግባርና ኃላፊነት

1. የተማሪ ወላጅ ማህበር ስትራቴጂያዊ ዓላማዎች ይለያል
2. የተማሪ ወላጅ ማህበር ተልዕኮና ዓላማ ማሳካት የሚያስችል የወላጆችን የሥራ ፕሮግራሞች ያዘጋጃል
3. የተማሪ ወላጅ ማህበር አጠቃላይ ጉባኤና የሥራ አስፈጻሚውን ኮሚቴ ስብሰባ ይመራል
4. የተማሪ ወላጅ ማህበር ሥራዎችን ያስተባብራል
5. ወላጆችን ከማህበረሰብና ከሴክተር መስሪያ ቤቶች በማገናኘት ኃላፊነቱን ይወጣል
6. ማህበሩን ወክሎ ይከሳል ይከሰሳል
7. ከምክትል ሊቀ መንበሩ እና ሂሳብ ሹም ጋር በጋራ በመሆን ፋይናንስን ይመራል

### 7.8.2. የምክትል ሊቀመንበር ተግባርና ኃላፊነት

1. ሊቀመንበሩ በማይገኝበት ወቅት እሱን ተክቶ ይስራል
2. የተማሪ ወላጆች ማህበርን ስትራቴጂያዊ ዓላማዎች ይለያል
3. ነባራዊ ሁኔታን ያገናዘበ ዕቅድ ከሊቀመንበሩ ጋር በመመካከር ያዘጋጃል
4. የተማሪ ወላጆች ማህበርን ተልእኮና ዓላማ ማሳካት የሚያስችል የወላጆች የሥራ ፕሮግራሞችና ፕሮጄክቶችን ይነድፋልህብት ያፈላልጋል
5. የተማሪ ወላጆች ማህበር ምክር ቤትና የሥራ አስፈጻሚውን ኮሚቴ ሊቀመንበርሩ በሌለበት በሰብሳቢነት ይመራል
6. መንግስታዊና መንግስታዊካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በቅንጅት ይሠራል
7. የተማሪ ወላጆች ማህበር ሥራዎችን ያስተባብራል
8. ወላጆችን ከማህበረሰብና ከሴክተር መሥሪያ ቤቶች በማገናኘት ኃላፊነቱን ይወጣል

### 7.8.3. የጸሐፊ ተግባርና ኃላፊነት

1. የተማሪ ወላጆች ማህበርን ስብሰባ አጀንዳዎችን ከሊቀመንበሩ ጋር በመመካከር አዘጋጅቶ ያቀርባል
2. የተማሪ ወላጆች ማህበርን ስብሰባ ቃለጉባኤ ይይዛል
3. የስብሰባውን ቃለጉባኤ በመመዝገብ አባላት ከሚቀጥለው ስብሰባ በፊት እንዲያውቁት ያደርጋል
4. ሌሎች የጥሪና በደብዳቤ የሚደረጉ ግንኙነቶችን በማዘጋጀት ያሰራጫል
5. የህብረቱን የጽሑፍ መዛግብትና ሌሎች መረጃዎች በማደራጀት ይይዛል
6. ሊቀመንበሩ እና ምክትል ሊቀ መንበሩ በማይገኙበት ወቅት ተክቶ ይሠራል

7. የማህበሩን ማህተም ይይዛል

### 7.8.4. የሂሳብ ሹም ኃላፍነትና ተግባር

1. የሂሳብ መረጃዎችን በመሰብሰብ ይተነትናል፣ሂሳብ በተያዘ የጊዜ ገደብ ይዘጋል
2. የወጪ ጥያቄዎች ሲቀርቡ ትክክልነታቸውን በማረጋገጥ ባግባቡ ያስተናግዳል
3. የሂሳብ መዛግብቶችን ያደራጃል
4. የሂሳብ ምርመራ ጥያቄ ሲቀርብ ሰነዶችን ያስመረምራል
5. ባመታዊ የዕቅድና በጀት ዝግጅት ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል
6. በበጀት አጠቃቀም ምክር ይሰጣል

### 7.8.5. ኦዲተር ኃላፊነትና ተግባር

1. የሂሳብ ምርመራ ወይም ኦዲቲንግ ዕቅድ ያዘጋጃል
2. የወጪ ትዕዛዞች በተያዘ የበጀት ዕቅድ መሆኑን ያረጋግጣል
3. የሂሳብ መዝገቦች በትክል መያዛቸውን ያረጋግጣል
4. የሂሳብ ሰነዶችን በተያዘ ዕቅድ መሰረት ይመረምራል
5. የሂሳብ ሪፖርቶችን በማዘጋጀት ለምክር ቤቱ በየግማሽ ዓመት ያቀርባል
6. በሂሳብ አያያዝ ወይም አሠራር ምክር ለሚመለከተው ይሰጣል

### 7.8.6. የገንዘብ ያዥ ተግባርና ኃላፊነት

የማህበሩ ገንዘብ ያዥ ተጠሪነቱ ለሥራ አስፈጻሚው ሆኖ የሚመረጠው ወላጅ ኃላፊነት የሚሰማውና ተአማኒ መሆን ይኖርበታል ፡፡

1. የተማሪ ወላጆች ማህበርን ሂሳብ ይይዛል ስለ ገንዘቡም ሪፖርት ያደርጋል
2. ትክክለኛ የወጪና የገቢ የሂሳብ ሰነዶችን መዝግቦ ይይዛል
3. በሚመለከተው አካል በታዘዘ ጊዜ የወጪና ገቢ ክፍያዎችን ይፈጽማል
4. ገቢ ሂሳቦችን በዕለቱ በባንክ ገቢ ያደርጋል ወርኃዊ የባንክ የሂሳብ ሪፖርቶችን መዝግቦ ይይዛል
5. ሂሳቡን በተፈለገ ጊዜ ኦዲት ያስደርጋል

## 7.9. በትምህርት ቤት ደረጃ የወተመህ ምክር ቤትና ስራ አስፈጻሚ አደረጃጀት

1. በየክፍሉ ያሉ የወተመህ ኮሚቴ አባላት የት/ቤት የወተመህ ምክር ቤት አባል ይሆናሉ
2. የት/ቤት ወተመህ የራሱ የሆነ ስራ አስፈፃሚ ይኖረዋል
3. የስራ አስፈፃሚ አባላት ብዛት እንደ ትምህርት ቤቱ ስፋትና በዝቅተኛ ከአምስት እስከ ሰባት ከፍተኛው ከዘጠኝ እስከ አስራ አንድ አባላት ይኖረታል
4. በዴሞክራሲያዊ አግባብ የተመረጠ የወተመህ ስራ አስፈጻሚ የስራ ዘመን ሦስት ዓመት ይሆናል፣የማኅበሩ አባላት ፍቃደኛ ከሆኑና ምክርቤቱ ከመረጣቸው በድጋሚ ለአንድ የምርጫ ዘመን ብቻ ሊያገለግሉ ይችላሉ

### 7.10. የትምህርት ቤት ወላጅ ተማሪ መምህር ህብረት ወተመሕ ወይም ወመህተግባር እና ኃላፊነትና

የትምህርት ቤት ወላጅ ተማሪ መምህር ህብረት በሁለት መዋቅር ይደራጃል፣ ይሄውም በጠቅላላ የወላጆች ጉባኤ ወይም በሴክሽንና በክፍል ደረጃ በሚደረግ ምርጫ የሚመረጥ የወተመህ ወይም ወመህ ምክር ቤትና የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ናቸው።

#### 7.10.1. የትምህርት ቤት የወተመህ፣ወመህ ምክር ቤት ኃላፊነትና ተግባር

የትምህርት ቤት የወተመህ፣ወመህ ምክር ቤት አባላት ከወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ከተማሪዎችና ከመምህራን የተመረጡ አባላትን ያቀፈ አካል ነው። ምክር ቤቱ እንደ ትምህርት ቤቱ የክፍል ብዛት የሚወሰን ሆኖ ከእያንዳንዱ ክፍል የወተመህ፣ወመህ ስድስቱ አመራሮች የትምህርት ቤቱ የምክር ቤቱ አካላት ይሆናል። ምክር ቤቱ በትምህርት ዓመቱ መጀመሪያ አጋማሽና በዓመቱ የትምህርት ማጠቃልያ የሚሰበሰብ ሆኖ ምክር ቤቱ የሚከተሉት የወል ኃላፊነቶችና ተግባራት ይኖሩታል።

1. የወላጅ ተማሪ መምህር ህብረት ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላትን ይሰይማል
2. ምክር ቤቱ ሥራውን በአስፈጻሚው ኮሚቴ አማካይነት ይከታተላል
3. የዓመቱን ዕቅድ ያጸድቃል አፈጻጸሙን ይገመግማል
4. ትምህርት ቤቱ በለያቸው ችግሮች ላይ መፍትሄ ይሰጣል
5. የንዑሳን ኮሚቴዎችን አባላት ይመርጣል
6. ከወከላቸው አባላት መካካል አመኔታ ያጣባቸውን ይሽራል አዲሶችም ይተካል

#### 7.10.2. የትምህርት ቤቱ ወላጅ ተማሪ መምህር ህብረት ወይም ወመህ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ

የወላጅ ተማሪ መምህር ህብረት ፣ወመህ ተጠሪነቱ ለምክር ቤቱ ሆኖ የሥራው ዘመን ሦስት ዓመት ይሆናል ። አባላትም ለሁለት ጊዜ ሊመረጡ ይችላሉ ። ሆኖም ምክር ቤቱ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ስራውን ባግባቡ ያልሰራና የሥነ-ምግባር ጉድለት ሲገኝበት በመገምገም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በማንኛውም ጊዜ አባላቱን ሊለውጥ ወይም ሊሽር ይችላል። ሥራ አስፈጻሚው የሚከተሉት ኃላፊነቶችና ተግባራት በወል ይኖሩታል።

1. የትምህርት ቤት ዓመታዊ ዕቅድና የማስፈጸሚያ ስልቶች እንዲሁም ሌሎች የውስጥ መመሪያዎች ሲነደፉ መሳተፍ

2. የትምህርት ቤት ዓመታዊ ዕቅዱን በታቀደው መሰረት መፈጸሙን መከታተል ፣ለተፈጻሚነቱም ድጋፍ መስጠት

3. ከተግባርና ኃላፊነታቸው ጋር የተያያዙ የሥራ ዕቅዶችን በማዘጋጀትና ለአፈጻጸም ለትምህርት ቤቱ ርእሰ መምህር በማቅረብ ተግባራዊ ማድረግ

4. የተዘጋጀውን የወተመህ ዕቅድ በዓመቱ መጀመሪያ በወላጆች መምህራን ጉባዔ ማስወሰን፣የዕቅድ ክንውኑም በዓመቱ አጋማሽ እና መጨረሻ ለጉባኤው ማቅረብ

5. መምህራን የሚጠበቅባቸውን የማስተማር ተግባር በትክክል መፈጸማቸውን ማረጋገጥ

6. ሙያዊ ኃላፊነታቸውን በአግባቡ የማይወጡትን መምህራን በመምከር ማስተካከል

7.ሙያዊ ኃላፊነቱን በአግባቡ የማይወጣ ርዕሰ መምህር በመምከር ማስተካከል፣በምክር የማይመለስ ከሆነ ጉዳዩን ለቀበሌው ወይም ለወረዳው የትምህርትና ሥለጠና ቦርድ አመራር ማቅረብ፣ በወረዳ ደረጃ ችግሩ መፍታት ካልተቻለ ወደ በላይ የመንግስት መዋቅር ጥያቄው ቀርቦ ችግሩ እንዲፈታ ይደረጋል

8. በትምህርት ቤት ደረጃ ሊወሰኑ የሚገባቸውን የመምህራንና ሠራተኞች የዲስፕሊን ጉድለትና ሌሎች ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ካልተሰጠ ጎብረቱ በቀጥታ ለቀበሌ ለወረዳ የትምህርት ሥለጠና ቦርድ አቅርቦ አፋጣኝ ውሳኔ እንዲሰጥበት ማመቻቸት፣ በወረዳ ደረጃ ችግሩ መፍታት ካልተቻለ ወደ በላይ የመንግስት መዋቅር ጥያቄው ቀርቦ ችግሩ እንዲፈታ ይደረጋል

9. ተማሪዎች በመልካም ሥነ ምግባር እንዲታነጹ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፣ የሥነ ምግባር ጉድለት ያለባቸውን ተማሪዎች መምከርና መገሰጽ

10. ትምህርት ቤቶችንና ወላጆችን በማሳተፍ የማህበረሰቡን ባህልና ወግ እንዲሁም ከትምህርት ሥራ ግንኙነት ያላቸው መመሪያዎችን መሰረት ያደረገ የትምህርት ቤት ውስጥ ደንብ ማውጣት ለህብረተሰቡ ማሳወቅ

11. የትምህርት ቤት መሻሻል ፕሮግራምና ሌሎች የትምህርት ጥራት ማስጠበቂያ መርሀ ግብሮች በትምህርት ቤቱ ተግባራዊና ውጤታማ እንዲሆኑ ንቁ ተሳትፎ ማድረግ

12. የትምህርት ቤቱ የውስጥ ገቢ የሚዳብርበትን መንገድ ከትምህርት ቤቱ አስተዳደርና ከቀበሌው ወይም ከወረዳው የትምህርት ስልጠና አመራር ቦርድ ጋር በመሆን ወላጆች አስፈላጊውን ተሳትፎ እንዲያደርጉ ማስተባበር

13. በትምህርትቤቱ ለትምህርት ሥራ የተመደበ ሀብት በአግባቡና በተጠያቂነት ሥራ ላይ እንዲውል ክትትልና ድጋፍ ማድረግ ፣ችግሮች ሲያጋጥሙ በደብዳቤ ለተቋሙ የማሳወቅና አፈጻጸሙን መከታተል ፣ የተለየው ችግር በትምህርት ቤቱ አመራር የማይፈታ ከሆነ በቀጥታ ለቀበሌ ለወረዳ የትምህርት ሥለጠና ቦርድ አቅርቦ አፋጣኝ ውሳኔ እንዲሰጥበት ማመቻቸት፣ በወረዳ ደረጃ ችግሩ መፍታት ካልተቻለ ወደ በላይ የመንግስት መዋቅር ጥያቄው ቀርቦ ችግሩ እንዲፈታ ይደረጋል

14. ወላጆች በመምህራን የሥራ አፈጻጸም ግምገማ ላይ እንዲሳተፉ ማድረግ

15. አርአያነት ያለው ተግባር ላከናወኑ መምህራንና ፣ሠራተኞች ፣ ወላጅ እና ተማሪዎች ከርዕሰ መምህሩ ጋር በመሆን ማበረታቻ እንዲያገኙ ማድረግ

16. የወላጆች የርዕሰ መምህራን እና የቀበሌው ወይም የወረዳው የትምህርትና ሥለጠና አመራር ቦርድ ግንኙነት ተጠናክሮ በጋራ እንዲሰሩ ሁኔታዎችን ማመቻቸት

17. ተማሪዎች ትምህርታቸውን እንዳያቋርጡ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣ ትምህርታቸውን ያቋረጡ የተማሪ ወላጆችን በማወያየት መፍትሄ መፈለግ

18. ከቀበሌ ወይም ወረዳ ትምህርትና ሥለጠና አመራር ቦርድ ጋር ጥብቅ ቁርኝት በመፍጠር ትምህርት ቤቱን ይከታተላል

### 7.10.3. የትምህርት ቤት የወላጅ ተማሪ መምህር ህብረት፣ወመህ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት

የኮሚቴው አባላት ብዛት እንደየ ትምህርት ቤቱ መምህራን ቁጥር የወላጅ መምህር ጥምርታ መሰረት የአባላት ብዛት ከ9 ሳያንስ ከአስራ አንድ ሳይበልጥ ሊቋቋም ይችላል። የተማሪና የመምህራን ተወካዮች የሚመረጡት ለተማሪዎች በትምህርት ቤቱ የተማሪዎች ፓርላማ ወይም በተማሪዎች ምክር ቤት ሲሆን የመምህራን በትምህርት ቤቱ መምህራን ማህበር የሚወከል ይሆናል። በኮሚቴው ውስጥ ከሁለት ተማሪ ተወካዮች አንድ ሴት ትሆናለች፣፣ በተመሳሳይ ከመምህራን ተወካዮች ግማሽች ሴቶች ይሆናሉ።

በምክር ቤቱ የሚመረጥ ወላጅ.....................................ሊቀመንበር

በምክር ቤቱየሚመረጥ መምህር...............................ምክትል ሊቀመንበር

በምክር ቤቱ የሚመረጥ መምህር ................................ጸሐፊ

በምክር ቤቱ » » » ወላጅ....................................ገንዘብ ያዥ

በምክር ቤቱ » » » መምህር.................................ሂሳብ ሹም

በምክር ቤቱ » » » ወላጅ ወይም መምህር........ ኦዲትና ኢንስፔክሽ

የተቀሩት የወላጅም ሆነ የመምህራን ተወካዮች...........አባልና የንኡሳን ኮሚቴዎች ተጠሪ ይሆናሉ፣

### 7.10.4. በትምህርት ቤት ደረጃ የክፍል የወተመህ ኮሚቴ አደረጃጀት

ይህ ኮሚቴ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ባሉ ተማሪዎች፣ ወላጆችና በክፍል ኃላፊው እንዲሁም ክፍሉ ከ5ኛ በላይ ከሆነ በተማሪ የክፍል አለቃ ወይም ተጠሪ ይዋቀራል፡ ተጠሪነቱም ለት/ቤቱ የወተመህ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ይሆናል ::

**አደረጃጀቱም፡-**

ሀ/ የተማሪ ወላጅ--------------- ብዛት ሶስት(አንድ ሰብሳቢ እና ሁለት አባላት)

ለ/ የክፍል ቤተ መምህር----------- አንድ ፀሐፊ

ሐ/ የክፍል ተማሪዎች ተጠሪ------- 1 አባል (ከ5ኛ ክፍል በላይ ከሆነ)

መ/ የክፍል ተማሪ ሴት ተወካይ-----1 አባል (ከ5ኛ ክፍል በላይ ከሆነ)

ሠ/ ክፍሉ ከአምስተኛ ክፍል በታች ከሆነ አራት ወላጅ እና 1 የክፍል ኃላፊ መምህር ይሆናል፡፡

ለ/ የክፍል የወተመህ ኮሚቴ የስራ ቆይታቸው ለሁለት ዓመት ሆኖ የስራ አፈጻፀማቸው የተሻለ ሆኖ ከተገኘ በድጋሚ በመመረጥ ለ1 ዓመት ሊያገለግሉ ይችላሉ፡፡

### 7.10.5. የትምህርት ቤት የወላጆች ተማሪ መምህር ህብረት ወይም ወመህ ሰብሳቢ ተግባርና ኃላፊነት

1. የትምህርት ቤቱን ስትራቴጂያዊ ዓላማዎች ይለያል
2. የትምህርት ቤቱን ተልኮና ዓላማ ማሳካት የሚያስችል የወላጆችን የሥራ ፕሮግራሞች ያዘጋጃል
3. የትምህርት ቤቱን የወላጆች ህብረት አጠቃላይ ጉባዔ ምክር ቤትና የሥራ

አስፈጻሚውን ኮሚቴ ስብሰባ ይመራል

4. የትምህርት ቤቱን የወላጆች ህብረት ሥራዎች ያስተባብራል
5. ወላጆችን ከትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህራን ከትምህርት ቤቱማህበረሰብ በማገናኘት ኃላፊነቱን ይወጣል
6. ማህበሩን በመወከል በማናቸውም ቦታ ይወከላል
7. ማህበሩን ወክሎ ይከሳል ይከሰሳል
8. የማህበሩን ፋይናንስ ከምክትል ሊቀንበርና ከዋና ጸሐፊ ጋር በመሆን ይመራል
9. በወተመሀ ስም የባንክ ሂሳብ ከምክትል ሊቀንበርና ከገንዘብ ያዥ ጋር በመሆን በጣምራ ፊርማ የባንክ ሂሳብ ይከፍታል ያንቀሳቅሳል

## 7.10.6.የትምህርት ቤት የወላጆች ተማሪ መምህር ህብረት ምክትል ሰብሳቢ ተግባርና ኃላፊነት

1. ሰብሳቢ በማይገኝበት ወቅት እሱን ተክቶ ይሠራል
2. የወላጆች ማህበርን ስትራቴጂያዊ ዓለማዎች ይለያል፣ነባራዊ ሁኔታን ያገናዘበ ዕቅድ ከሰብሳቢው ጋር በመመካከር ያዘጋጃል
3. የወላጆች ማህበርን ተልዕኮና ዓላማ ማሳካት የሚያስችል የወላጆችን የሥራ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶችን ይነድፋል ሀብት ያፈላልጋል
4. የወላጆች ማህበር ምክር ቤትና የሥራ አስፈጻሚውን ኮሚቴ ሰብሳቢውን ወክሎ ይመራል
5. መንግሥታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በቅንጅት ይሠራል
6. የወላጆች ማህበር ሥራዎችን ያስተባብራል
7. ወላጆችን ከማህበረሰብና ከሴክተር መስርያ ቤቶች በማገናኘት ኃላፊነቱን ይወጣል
8. የማህበሩን ፋይናንስ ከሰብሳቢው እና ከሂሳብ ሹሙ ጋር በመሆን የባንክ ሂሳብ ይከፍታል ይመራል

## 7.10.7.የትምህርት ቤት የወላጆች ተማሪ መምህር ህብረት ጸሐፊ ተግባርና ኃላፊነት

1. የወላጆች ህብረት ስብሰባ አጀንዳዎችን ከሰብሳቢው ጋር በመመካከር አዘጋጅቶ ያቀርባል
2. የወላጆች ህብረት ስብሰባ ቃለጉባዔ ይይዛል
3. የስብሰባውን ቃለጉባዔ በመመዝገብ አባላት ከሚቀጥለው ስብሰባ በፊት እንዲያውቁት ያደርጋል
4. ሌሎች የጥሪና በደብዳቤ የሚደረጉ ግንኙነቶችን በማዘጋጀት ያሰራጫል
5. የህብረቱን የጽሁፍ መዛግብትና ሌሎች መረጃዎች በማደራጀት ይይዛሌ
6. ሰብሳቢው እና ምክትል ሰብሳቢው በማይገኝበት ወቅት ተክቶ ይሠራል
7. የወተመህን(ወመህ) ማህተም ይይዛል

## 7.10.8. የትምህርት ቤት የወላጆች ተማሪ መምህር ህብረት ሂሳብ ሹም ኃላፊነትና ተግባር

1. የሂሳብ መረጃዎችን በመሰብሰብ ይተነትናል፣
2. ሂሳብ በተያዘ የጊዜ ገደብ ይዘጋል፣
3. የወጪ ጥያቄዎች ሲቀርቡ ትክክለኛነታቸውን በማረጋገጥ በአግባቡ ያስተንግዳል ፣
4. የሂሳብ መዛግብቶችን ያደራጃል ፣
5. የሂሳብ ምርመራ ጥያቄ ሲቀርብ ሰነዶችን ያስመረምራል ፣
6. ዓመታዊ የዕቅድና በጀት ዝግጅት ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል፣
7. በበጀት አጠቃቀም ምክር ይሰጣል ፣

## 7.10.9 በትምህርት ቤት የወላጆች ተማሪ መምህር ህብረት ወይም የወላጅ መምህር

**ህብረት ኦዲተር ኃላፊነትና ተግባር**

1. የሂሳብ ምርመራ ወይም ኦዲቲንግ ዕቅድ ያዘጋጃል
2. የወጪ ትዛዞች በተያዘ የበጀት ዕቅድ መሆኑን ያረጋግጣል
3. የሂሳብ መዝገቦች በትክክል መያዛቸውን ያረጋግጣል
4. የሂሳብ ሰነዶችን በተያዘ ዕቅድ መሰረት ይመረምራል
5. የሂሳብ ሪፖርቶች በማዘጋጀት ለምክር ቤቱ በግማሽ ዓመት ያቀርባል
6. በሂሳብ አያያዝ ወይም አሠራር ምክር ለሚመለከተው ይሰጣል

## 7.10.10 የትምህርት ቤት የወላጅ ተማሪ መምህርህብረት ወይም የወላጅ መምህር ህብረት

### ገንዘብ ያዥ ተግባርና ኃላፊነት

የህብረቱ ገንዘብ ያዥ ተጠሪነቱ ለስራአስፈፃሚው ሆኖ የሚመረጠው ወላጅ ሃለፊነት የሚሰማውና ተአማኒ መሆን ይኖርበታል፡፡

1. የወተመህ/ወመህ ሂሳብ ይሰበስባል፣ ይይዛል፣ለስገንዘቡ ሪፖርት ያደርጋል
2. ትክክለኛ የወጪና የገቢ የሂሳብ ሰነዶችን መዝግቦ ይይዛል
3. በሚመለ ከተው አካል በታዘዘ ግዜ የወጪና ገቢ ክፍያዎችን ይፈፅማል
4. ገቢ ሂሳቦችን በዕለቱ በባንክ ገቢ ያደርጋል፣ ወርሃዊ የባንክ የሂሳብ ሪፖርቶችን መዝግቦ ይይዛል
5. ሂሳቡን በተፈለገ ጊዜ ኦዲት ያስደርጋል

## 8. የወተመህ /ወመህ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

### 8.1 በትምህርት ቤት የየክፍሉ ወተመህ /ወመህ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለትምህርት ቤቱ የወተመህ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሯታል

1. በክፍሉ ውስጥ የሚያከናውናቸው ዓመታዊ የግማሽ ዓመት የሩብ ዓመት የየወሩን ተግባራት ያቅዳል በክፍሉ እንዲፀድቅ ያደርጋል
2. በክፍሉ ውስጥ የሶስትዩሽ ፎርማ ከወላጅ ፣ከመምህሩና ከተማሪ ጋር እንዲፈራረሙ ያደርጋል፣ይከታተላል
3. ለክፍሉ አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶች እንዲሟሉ ጥረት ያደርጋል
4. ተማሪዎች በትምህርታቸው ውጤታማ እንዲሆኑ ፣እንዳያቋርጡ እና እንዳይደግሙ ያወያያል ይመክራል በመልካም ስነ-ምግባር እንዲታነፁ ያደርጋል
5. የተለያዩ የተማሪዎች የተማሪ አደረጃጀቶችና ክበባት እንዲደረጁና ውጤታማ እንዲሆኑ ጥረት ያደርጋል
6. የተለያዩ የተማሪዎች የተማሪ አደረጃጀቶች ክበባት እንዲደረጁና ውጤታማ እንዲሆኑ ጥረት ያደርጋል
7. በተማሪና በመምህሩን መካከል ያለው ግንኙነት ጤናማ እንዲሆንና የመማር ማስተማሩ ሂደት ውጤታማ እንዲሆን የውይይት ፕሮግራም ያዘጋጃል፣ያወያያል ችግር ካለ ይፈታል
8. ከኮሚቴው አቅም በላይ የሆኑ ችግሮችን አጥንቶ ለስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ እና ለትምህርት ቤቱ አስተዳደር ያቀርባል

9. ከትምህርት ቤቱ ወተመህ ምክር ቤት ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚሰጠውን ተጨማሪ ተግባር ያከናውናል

**9. የመንግስት የግልና መንግሥታዊ ያልሆኑ የትምህርት ተቋማት የወተመህ /ወመህ የሥራ አስፈፀሚ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት**

ተጠሪነቱ ለት/ቤቱ ወተመህ/ወመህ ምክር ቤትና ጠቅላላ ጉባዓ ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት አለው

1. በትምህርት ቤት ደረጃ የሚከናወኑ የዓመት የግማሽ ዓመት የሩብ ዓመት እና የወር ተግባራትን ያቅዳል በምክር ቤቱ ያፀድቃል
2. በየክፍሉ የተቋቋሙ የወላጅ ኮሚቴዎች በእቅዳቸው መሰረት እየሰሩ መሆኑን ይከታተላል ይደግፋል፣ ይቆጣጠራል
3. ከየክፍሉ ወተመህ ኮሚቴ ተጠንተው የሚቀርቡ ጉዳዩች ይመረምራል መፍትሄ ይሰጣል
4. ወላጆችና አሳዳጊዎች በልጆቻቸው ትምህርት ጉዳዩች በንቃት በመሳተፍ የተማሪዎች እና መማር ማስተመሯ እንዲጎለብት የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ ምቹ ሁኔታ መፈጠሩን ያረጋግጣል
5. ለመንግስት ትምህርት ቤት ህብረተሰቡን በማስተባበር የትምህርት ቤት ገቢ እንዲዳብር ያደርጋል፤ ለመማር ማስተማሪ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል
6. በምዘና በመሳተፍ አርአያነት ያለው ተግባር ላከናወኑ፤ የላቀ የተማሪዎች ውጤት እንዲመዘገብ አስተዋፅኦ ላደረጉ መምህራን፤ ሰራተኞችና ወላጆች ከርዕሰ መምህሯ ጋር በመሆን ማበረታቻ ሽልማት እንዲሰጥ ያደርጋል
7. የት/ቤቱ ትምህርት አሰጣጥ የአገሪቱን የትምህርት ፖሊሲና ሥርዓት መሠረት ያደረገ መሆኑን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል
8. የአጠቃላይ የትምህርት ጥራት ፓኬጅ ፕሮግራሞች በትምህርት ቤት በተሟላ ሁኔታ በመተግበር የላቀ የተማሪዎች ውጤት ማስመዝገቡን ያረጋግጣል
9. ተማሪዎች በመልካም ሥነ- ምግባር እንዲታነፁ ከወላጆች፣ ከት/ቤቱ አስተዳደርና ከተማሪዎች ጋር ጠንካራ ግንኙነት በመመስረት ይከታተል
10. የትምህርት ቤትና የወላጅ ጤናማ ግንኙነትን ለማጠናከር ልዩ ልዩ ዘዴ በመቀየስ ተግባራዊ ያደርጋል
11. ከመምህራንና ከትምህርት ቤቱ አስተዳደር አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከተማሪዎች ጋር በመወያየት የትምህርትን አሰጣጥ ምልካም ውጤት እንዲያስገኝ ከማድረግ አንጻር ትኩረት ሰጥቶ ይሰራል
12. መምህራን እና የት/ቤቱ አስተዳደር የመማር ማስተማር ስራዎችን በትክክል እየፈፀሙ መሆናቸውን ይከታተላል ችግሮችን ያርማል፣ ያስተካክላል፣ ከአቅም በላይ የሆኑትን ጉዳዩች ለክ/ከተማ ያቀርባል

13. የትምህርት ጥራት ላይ ትኩረት በመስጠት የመማር ማስተማሩን ሂደት እንዲጎለብት የበኩሉን ሙያዊና ሌሎች አስፈላጊ አስተዋፅኦዎችን ያደርጋል

14. ት/ቤቱ ከሌሎች ትምህርት ቤቶች ጋር የቅርብ ግንኙነት እንዲፈጥርና የልምድ ልውውጥ እንዲያደርግ እገዛ ያደርጋል

15. የት/ቤቱ ተማሪዎች የት/ቤቱን ደንብና ሥርዓት እንዲያከብሩና ራሳቸውን ከጉጅ ባህሪያት እንዲያርቁ ይመክራል፣ይከታተላል፣ከት/ቤቱ አስተዳደር ጋር በመሆን ተገቢውን የእርምት ርምጃ ይወስዳል

16. የትምህርት ቤቱን ንብረት በአግባቡ መያዙንና መጠበቁን ከትምህርት ቤቱ አስተዳዳር እና ርእሰ መምህር ጋር በመሆን ተገቢዉን ቁጥጥርና ክትትል ያደርጋል፡፡ ባከኖ ከተገኘ በህግ ተጠያቂ ያደርጋል

17. በት/ቤቱ ስሚከሰቱት የዲሲፕሊን የፀጥታና ሌሎች ችግሮች ከት/ቤቱ አስተዳደርና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ወገኖች ጋር በመሆን መፍትሔ ይሻል፣ ተገቢውን ሕጋዊ ርምጃ ይወስዳል፣ እንዲወሰድም ያደርጋል

18. በትምሀርት ቤቱና  በወላጆች /አሳዳጊዎች መካከል የሚፈጠር ውጤታማ ግንኙነት የተማሪዎችን መማር የሚያበረታታና የሚያግዝ እንዲሆን ስልት ቀይሶ ይሰራል ፣

19. ኮሚቴው በወር ሁለት ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል አስፈላጊ ሲሆን በመሃል አስቸኳይ ጉባኤ ሊጠራ ይችላል

20. ወላጆችና ተማሪዎች በመወከል የወላጆችንና የተማሪዎችን ሐሳብ፣ቅሬታ አቤቱታ ጥያቄና የመሳሰሉትን ከት/ቤቱ አመራር ጋር በመነጋገር መፍትሔ እንዲያገኝ ያደርጋል፣አፈጻፀሙን ይከታተላል

21. ከት/ቤቱ አመራር ጋር በመነጋገር አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የወላጆች ጠቅላላ ጉባኤ ይጠራል፣ሪፖርት ያቀርባል

22. በግልና በመንግስታዊ ያልሆኑ ትምህርት ቤቶች ት/ቤቱ የክፍያ ለውጥ ለማድረግ ማቀዱ (መፈለጉ) ሲረጋገጥ የጭማሬውን አግባብነት አስመልክቶ ከት/ቤቱ ጋር ይወያያል አግባብነቱን ለወላጆች ያሳውቃል አግባብነት የለሌውን ምክንያታዊ ያልሆነ ጭማሬ ከሆነ የትምህርት ቤቶች ክፍያ በተመለከተ ሐምሌ 2007 በመመሪያ ቁጥር 1/2007 ባወጣ የግል ትምህርት ተቋማት የትምህርት አገልግሎት አሰጣጥና ክፍያ ስርዓት መመሪያ አንቀፅ 5፣6 እና 7 መሰረት ብቻ ተፈፃሚ ይደረጋል፡፡ ሆኖም ግን በት/ቤቱ የገንዘብ አያያዝና አጠቃቀም ውስጥ በማናቸውም መልኩ ጣልቃ አይገባም

23. አርአያነት ያለው ተግባር ለሚፈጽሙ ወላጆች መምህራን፣ ሠራተኞችና ተማሪዎች አመራሮች ከት/ቤቱ አስተዳደርና ወላጆች ጋር በመመካከር የማትጊያ ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል

24. የት/ቤቱ አስተዳደርና መምህራን ሙያዊ በሆነ ስነ-ምግባር አክብረው ግዴታቸው እየተወጡ ስለመሆናቸው ይከታተላል፣እርምጃ ይወስዳል

25. ትምህርት ቤቱ ከሌሎች ት/ቤቶች ጋር ግንኙነት በመፍጠር መልካም ተሞክሮ የሚቀስምበትን መንገድ ያመቻቻል፣ ያግዛል፣ ተግባራዊም ያደርጋል

26. ለዓመቱ የተመደበው ስርዓተ- ትምህርት በታቀደለት ጊዜ እንዲከናወን ከት/ቤቱ አስተዳደር ጋር በመሆን በየጊዜው ይከታተላል፣አፈፃፀሙን ያረጋግጣል

27. በት/ቤቱና በወላጆች መካከል ድልድይ በመሆን ግንኙነት እንዲጠናከርና የመማር ማስተማሩ ሥራ የተሳካ እንዲሆን ያላሰለሰ ጥረት ያደርጋል

28. በግልና መንግስታዊ ባልሆነ ትምህርት ቤቶች የውጭ ዜግነት ያሏቸው መምህራንና ሰራተኞች በተቋሙ ሲቀጠሩ ከሚመለከተው አካል የስራ ፍቃድ ማግኘታቸውን ያረጋግጣል፡፡ በተቋሙ ውስጥም ካለስራ ፈቃድ  የመማር ማስተማሩን ሂደት የሚያከናውኑ ካሉ  ስራቸውን እንዲቋርጡ ያደርጋል ለሚመለከተው  አካልም መረጃ ያቀርባሉ

29. የትምህርት ቤቱን የሥራ እንቅስቃሴዎች በመልካምነታቸውና በጠቃሚነታቸው ለህብረተሰቡ የማስተዋወቅ ሥራ በመስራት ትም/ቤቱ ሥራ ላይ የማህበረሰቡ ግንዛቤ እንዲዳብር የሕዝብ ግንኙነት ስራ ይሰራል

30. ሌሎች ትምህርት ቤቱን የሚመለከቱ ስራዎችን እንደ አንድ የትምህርት ቤቱ አመራር አካል በመሆን በሃላፊነት ይሰራል

31. አዋኪ በሆኑ የትምህርት ችግሮች ላይ መፍትሄ ያፈላልጋል

**10. በትምህርት ቤት ደረጃ የወተመህ/ወመህ ምክር ቤት ተጠሪነቱ ለወረዳው የወተመህ ምክር ቤት ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖረታል**

1. የወተመህ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ያቀረበውን እቅድ ይመረምራል፣ያፀድቃል፣
2. የወተመህ ስራ አስፈፀሚ ኮሚቴ ያከናወናቸውን ተግባርት ሪፖርት ይሰማል ገምግሞ ያፀድቃል፣
3. ከሁሉም ወላጆች ጋር የምክክር መድረክ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣ ያውያያል ስለተማሪ ውጤትና ባህሪ መሻሻል የጋራ ግንዛቤ እንዲኖር ያደርጋል፣

**11. የወረዳው ወተመህ ስራ አስፈፀሚ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለወረዳው ወተመህ ምክር ቤት ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖረታል**

1. በወረዳ ደረጃ የሚከናወኑ አመታዊ፣ የግማሽ ዓመት፣ የሩብ ዓመት እና የወር ተግባራትን ያቅዳል በምክር ቤቱ ያፀድቃል
2. በየትምህርት ቤቱ ያሉ ምክር ቤቶች ስራ አስፈፃሚዎች በእቅዳቸው መሰረት እየሰሩ መሆናቸውን ይከታተላል፣ ድጋፍ ይሰጣል
3. ከየትምህርት ቤቱ ከወተመህ ምክር ቤት የሚቀርቡ ጉዳዮችን ይመረምራል ውሳኔ ያሰጣል
4. የተማሪ ወላጆችንና ህብረተሰቡን በማስተባበር በትምህርት ቤቶች ለመማር ማስተማሩ ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠር ያደርጋል
5. አርአያነት ያለው ተግባር ላከናወኑ መምህራን ፣ር/መምህራን ሰራተኞች ወላጆችና ምክር ቤቶች የማበረታቻ ሽልማት እንዲሰጥ ያደርጋል

**12. በወረዳ ደረጃ የወተመህ ምክር ቤት ተጠሪነቱ ለክፍለ ከተማ የወተመህ ምክር ቤት ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል**

1. የወተመህ ስራ አስፈፃሚ ያቀረበው እቅድ ይመረምራል፣ያፅድቃል
2. የወተመህ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ያከናወናቸውን ተግባራት ሪፖርት ያዳምጣል ገምግሞ ያጸድቃል
3. በስሩ ከሚገኙ ምክር ቤቶች ጋር የጋራ መድረክ በማዘጋጀት ይመክራል የትኩረት አቅጣጫዎችን ያስቀምጣል

**13. የክፍለ ከተማ የወተመህ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለወተመህ ምክር ቤት ሆኖ የሚከተሉትን ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል**

1. በክፍለ ከተማ ደረጃ የሚከናወኑ ዓመታዊ፣ የግማሽ ዓመት የሩብ ዓመት እና የወር ተግባራትን ያቅዳል በምክር ቤቱ ያፀድቃል
2. በወረዳው ያሉ ምክር ቤቶችና የስራ አስፈፃሚዎች በእቅዳቸው መሰረት እየሰሩ መሆናቸውን ይከታተላል ድጋፍ ይሰጣል
3. ከየወረዳው የወተመህ ምክር ቤት የሚቀርቡ ጉዳዮች ሲኖር ይመረምራል ውሳኔ ይሰጣል
4. በስሩ ባሉ ወረዳዎች ያሉ የወተመህ ምክር ቤቶች ተማሪ ወላጆችና ህብረተሰቡን በማስተባበር ለመማር ማስተማሩ ስራ ምቹ ሁኔታ መፍጠራቸውን ያረጋግጣል
5. ለትምህርት ጥራት መሻሻል ከፍተኛ ስራ ለሰሩ መምህራና ሰራተኞች ርዕሰ መምህራንና የወተመህ ምክር ቤት አባላት የማትጊያ ሽልማት እንዲያገኙ ያደርጋል
6. የልምድ ልውውጥ መድረክ ያዘጋጃል ያስፈፅማል
7. ከወተመህ ምክር ቤት የሚሰጠው ተጨማሪ ተግባራት ያከናውናል

## 14. የከተማ የተወማ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለተወማ ምክር ቤት ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖረታል

1. በከተማ ደረጃ የሚከናወኑ ዓመታዊ ፣የግማሽ ዓመት የሩብ ዓመት እና የወር ተግባራትን ያቀዳል በምክር ቤቱ ያፀድቃል፣
2. በየክፍለ ከተማው ያሉ ምክር ቤቶችና ስራ አስፈፃሚዎች በዕቅዳቸው መሰረት እየሰሩ መሆናቸውን ይከታተላል፣ድጋፍ ይሰጣል፣
3. በየክፍለ ከተማው የወተመህ ምክር ቤት የሚቀርቡ ጉዳዮችን ይመረምራል ውሳኔ ይሰጣል፣
4. በሁሉም ክፍለ ከተማ ያሉ የወተመህ ምክር ቤቶች የተማሪ ወላጆች ህብረተሰቡን በማስተባበር ለመማር ማስተማሪያ ስራ ምቹ ሁኔታ መፍጠራቸውን ያረጋግጣል፣
5. ለትምህርት ጥራት መሻሻል ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረጉ መምህራንና ሰራተኞች፣ ር/መምህራን ወላጆች የምክር ቤት አባላትን በማወዳደር ለትምህርት ቢሮ በማቅረብ የማበረታቻ ሽልማት እንዲገኙ ያደርጋል፣
6. የልምድ ልውውጥ መድረክ ያዘጋጃል ያስፈፅማል፣
7. ከወተመህ ምክር ቤት የሚሰጠውን ተጨማሪ ተግባራት ያከናውናል፣

## 15. የከተማ የተወማ ምክር ቤት ተግባርና ኃላፊነት

1. የተወማ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ያቀረበውን እቅድ ይመረምራል ፣ያፀድቃል
2. የተወማ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ያከናወናቸውን ተግባራት ሪፖርት ያዳምጣል ገምግሞ ያፀድቃል
3. በስሩ ከሚገኙ ምክር ቤቶች ጋር የጋራ መድረክ በማዘጋጀት ይመክራል የልምድ ልውውጥ እንዲደረግ ያደርጋል
4. የተሻለ አፈፃፀም ያላቸውን የክፍለ ከተማ የተወማ ምክር ቤታችን በመለየት የልምድ ልውውጥ እንዲደረግ ያደርጋል

## 16. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተወማ/ወተመህ/ወመህ/ ንዑሳን ትምህርት ዘርፍ በየደረጃው ያሉ አካላት ኃላፊነትና ተግባር

### 16.1. የንዑሳን ኮሚቴዎች ሃለፊነቶችና ተግባራት

ከሃገር አቀፍ እስከ ትምህርት ቤት ደረጃ የሚዋቀረው የወላጆች ማህበር ከተሠጠው የስራ ሃለፊነትና ተግባር አንፃር ስራዎችን ለማቀላጠፍና ለጸቶ ለመስራት በትምህርት ቤት ደረጃ የሚከተሉት ንዑሳን ኮሚቴዎችን ና ሌሎችንም እንደየአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ጥናት በማድረግ ሊያደራጅ ይችላል፡፡ስራውንም በቅንጅት ለመምራትና የክንዋኔውን አፈፃፀም ሪፖርት ማድርግ እንዲቻል በየደረጃው ከሚገኙ ስራ አስፈፃሚ አባላት መካከል ለሚቋቋሙት ንዑሳን ኮሚቴዎች

አንድ አንድ ተጠሪዎች በየደረጃውዩ መድባል፡፡ምክር ቤቱ አባላቱን ከወላጆች ከተማሪዎችና ከመምህራን መካከል ለእያንዳንዱ ንዑስ ኮሚቴ አባላትን ይመርጣል፡፡አባላቱ የራሳቸውን ሰብሳቢ ፀሃፊና አባላትን ይሰይማሉ፡፡

## 16.2 የሰላምና ደህንነት ንዑስ ኮሚቴ የስራ ሀላፊነትና ተግባራት

የሰላምና ደህንነት ንዑሥ ኮሚቴ 5 አባላት ሲኖሯት በት/ቤቱ ምክር ቤት ይሰየማሉ ኮሚቴው ተጠሪነቱ ለምክር ቤቱና ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሆኖ አንድ ሰብሳቢና አንድ ፀሃፊ ይኖሯታል፡፡

1.ኮሚቴው አመታዊ እቅዱን እያወጣ ሲያፀድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

2.ኮሚቴው በትምህርት ቤቶች አካባቢ የተማሪዎች ሰላምና ደህንነት የሚጠበቅበትን ስልት እየቀየሰ ለየደረጃው የትምህርት መዋቅር አቅርቦ ከስምምነት ሲደርስ በየደረጃው ባሉት ወላጆች ማህበር ያስተሳፍል ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፡፡

3. በትምህርት ቤት የተማሪዎች ጤንነት የሚጠበቅበትን ስልት ከት/ቤት ከቀበሌ ወይም ከወረዳ ት/ፅ/ቤት ጋር በመሆን የጋራ አቅጣጫዎችን ይነድፋል፡፡

4.ተማሪዎች በሰው ሰራሽና በተፈጥሮ አደጋዎች ሲያጋጥሟቸው የሚችሉትን ችግሮች ፈጥኖ በመገንዘብ ከት¤ቤት ከቀበሌ ወረዳና ከትምህርት ፅፈት ቤት ጋር በመሆን የመፍትሄ ሃሳቦችን ይሰጣል፡፡

5.በየደረጃው በሚቋቋሙ ወላጆች ማህበራት ጋር በመሆን የሰላምን ፋይዳ ለተማሪዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች ይሰራል፡፡

6. ታወቂ ግለሰቦችና የሃገር ሽማግሌዎችን በትምህርት ቤት በመጋበዝ በግብረ ገብነትና በመልካም ስነምግባር መርሆዎች ላይ ለተማሪዎች ት/ቤት እንዲሰጥ በየደረጃው ካለው አደረጃጀት ጋር ይሰራል፡፡

7. ኮሚቴው ስለስራው እቅድ አፈፃፀም ለስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በየሩብ አመት ሪፖርት ያደርጋል፡፣

## 16.3. የመማርና ማስተማር ንዑስ ኮሚቴ የሥራ ኃላፊነትና ተግባር

የመማርና ማስተማር ንዑስ ኮሚቴ 5 አባላት ሲኖሩት በትምህርት ቤት ምክር ቤት ይሰየማል ። ኮሚቴው ተጠሪነቱ ለሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሆኖ አንድ ሰብሳቢና አንድ ጸሐፊ ይኖሩታል።

1.ኮሚቴው ዓመታዊ ዕቅዱን እያወጣ ሲጸድቅ ተግባራዊያደርጋል

2. በትምህርት ቤቶች አካባቢ የሚካሄደውን አጠቃላይ የመማር ማስተማር ሂደቶችን በየደረጃው በተቋቋሙት አደረጃጀቶች አማካኝነት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን በትምህርት ቤቶች ውስጥ ትግበራውን ይከታተላል ይገመግማል፣

3. ወላጆች የልጆቻቸው ትምህርት ውጤትና ባሕሪ የሚሻሻልበ ትን መንገድ እንዲያውቁና ልጆቻቸውን እንዲያግዙ ስልጠናዎች የሚመቻችበትን ሁኔታ ከትምህርት ቤት ከቀበሌ ወይም ከወረዳ ትምህርትና ሥለጠና ቦርድ ጋር በመሆን ይሠራል፣

4.በተማሪና ወላጆች መካከል የጋራ መድረክ እንዲፈጠር ሁኔ ታዎችን ያመቻቻል ፣
ሰ. ኮሚቴው በትምህርት ቤት ከተቋቋሙ መሰል ኮሚቴዎች «ትምህርት ቤት መሻሻያ ኮሚቴ…» ጋር በጋራ ይሠራል ፣፣

5. ኮሚቴው ስለሥራው ዕቅድ አፈጻጸም ለሥራ አስፈጻሚው ኮሚቴ በየሩብ ዓመቱ ሪፖርት ያደርጋል ፣

## 16.4.የትምህርት ሃብት ማፈላለግና ማጎልበት ንዑስ ኮሚቴ የሥራ ኃላፍነትና ተግባር

የትምህርት ሀብት ማፈላለግና ማጎልበት ንዑስ ኮሚቴ 5 አባላት ሲኖሩት በጠቅላላ ጉባዔው ይሰየማል ፡፡ ኮሚቴው ተጠሪነቱ ለሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሆኖ አንድ ሰብሳቢና አንድ ጸሐፊ ይኖሩታል፡፡

1. ኮሚቴው ዓመታዊ እቅዱን እያወጣ ሲጸድቅ ተግባራዊ ያደርጋል

2. ትምህርት ቤቶች የሚደገፉበትን ሀብት ከወላጆችና ከባልደረሻ አካላት የሚገኝበትን ስልት በመንደፍ ስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል

3. ለትምህርት ቤቶች የሚደረገው ድጋፍ በህጋዊነት በተፈቀደ አግባብ እንዲፈጸምና እንዲጎለብት ይሰራል

4. ማንኛውም የትምህርት ቤት ሀብት ባለው ህጋዊ የመንግሥ ት አሰራር ለታለመለት ዓላማ እንዲውል ከትምህርት ቤቱ ጋር በጋራ ይሰራል

5. ኮሚቴው ስለስራው እቅድ አፈጻጸም ለስራ አስፈጻሚው ኮሚቴ በየሩብ ዓመት ሪፖርት ያደርጋል

## 16.5 በየደረጃው የሚገኙ የትምህርት ቢሮ አደረጃጀቶች ኃላፊነቶችና ተግባራት

1. በየደረጃው የሚካሄዱትን የተማሪ ወላጆች ማህበር የምርጫ ሂደት ከጅምሩ እስከ ፍጻሜው ያስተባብራሉ፣ ስለ ሂደቱ ለበላይ ሪፖርት ያቀርባለ
2. የማህበሩን ሥራ ያግዛሉ፣ ይደግፋሉ ፣ ይተባበራሉ

3. በእቅድ አዘገጃጀትና አፈጻጸም ግምገማ ማህበሩን ያሳትፋሉ

4. ለማህበሩ መቀመጫ ቢሮ ያዘጋጃሉ

5. ለሥራ ማስኬጃ በጀት በማፈላለግ ይመድባል

## 16.6 የወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት በኮሚቴ ምርጫው ላይ ያለውን ኃላፊነትና ተግባር

1. በመንግስት ፣ ከግልና መንግስታዊ ካልሆኑ ትምህርት ቤቶች ጋር በመመካከር የወላጆች ጠቅላላ ጉባኤ ቅድመ መደበኛ ፣የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚካሄድበት ቀንና ቦታ ይወስናል

2. ትምህርት ጽ/ቤት በቦታውና በዕለቱ በመገኘት አስመራጭ ኮሚቴ ይሰይማል፡፡ የምርጫውን ዴሞክራሲያዊነት ይታዘባል፣ ሂደቱ ሲጠናቀቅም ሪፖርት ለክፍለ ከተማው ያቀርባል

3. ከመንግስት ፣ከግልና መንግስታዊ ካልሆኑ ትምህርት ቤቶች ጋር በመተባበር ለእያንዳንዱ ወላጅ ጥሪ መተላለፉን ያረጋግጣል፡፡ ችግር ሲያጋጥም ይፈታል

4. ስለ ወተመህ ሥልጣንና ተግባር አስፈላጊነት በምርጫው ቀን ለተሰብሳቢ ወላጆች ያሳውቃሉ ግንዛቤ ያስጨብጣሉ

## 16.7 የኮሚቴውን ስራ መደገፍና መከታተል ላይ ያለው ኃላፊነትና ተግባር

1. የወተመህ ኮሚቴን ስራ ይከታተላል ይደግፋል
2. በዕቅድ ዝግጅትና አፈፃፀም ግምገማ ኮሚቴውን ያሳትፋል
3. ችግሮች ሲከሰቱ ከትምህርት ቤቱ አስተዳደርና ባለኃብቱ ወይም ድርጅት ጋር በመነጋገር መፍትሄ ያፈላልጋል
4. በበጀት ፣በቁሳቁስ እና በቢሮ ይደግፋል

### 16.8 . የክፍለ ከተማ ትምህርት ጽ/ቤት ተግባርና ኃላፊነት

#### 16.8.1.1 በኮሚቴው ምርጫው ላይ ያለው ኃላፊነት

1. የተማሪ ወላጅ ማህበር ከመንግስት ከግልና መንግስታዊ ካልሆኑ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ጋር በመመካከር የወላጆች ጠቅላላ ጉባኤ የሚካሄድበትን ቀንና ቦታ ይወስናል
2. በቦታውና በዕለቱ በመገኘት አስመራጭ ኮሚቴ ይሰይማል ቀጥሎም ምርጫውን ዴሞክራሲያዊነት ይታዘባል፡ ሂደቱ ሲጠናቀቅም ሪፖርት ለከተማው ያቀርባል
3. ከመንግስት፣ከግልና መንግስታዊ ካልሆኑ ሁለተኛ ደረጃ መሰናዶ ትምህርት ቤቶች ጋር በመተባበር ለእያንዳንዱ ወላጅ ጥሪ መተላለፉን ያረጋግጣል ችግር ሲያጋጥም ይፈታል
4. ስለ ወተመህ ሥልጣንና ተግባር አስፈላጊነት በምርጫው ቀን ለተሰብሳቢ ወላጆች ያሳውቃሉ/ ግንዛቤ ያስጨብጣል

#### 16.8.1.2 የኮሚቴውን ስራ መደገፍና መከታተል ላይ ያለው ኃላፊነት ተግባር

1. የወተመህ ኮሚቴ ስራ ያስተባብራሉ ይደግፋል
2. በዕቅድ ዝግጅትና አፈጻፀም ግምገማ ኮሚቴውን ያሳትፋል
3. ችግሮች ሲከሰቱ ከትምህርት ቤቱ አስተዳደርና ባለሃብቱ ወይም ድርጅት ጋር በመነጋገር መፍትሄ ያፈላልጋል
4. በቢሮ በጀት ቁሳቁስ እና ከተውማ ጋር የተያያዙ መረጃዎችን በወቅቱ ማድረስ

## ክፍል ሦስት

## 17. የግንኙነት ፣የሪፖርትና የግብረ-መልስ አሰጣጥ ስርዓት አግባብ

1. በትምህርት ቤት በየክፍሉ የወተመህ ኮሚቴ በየወሩ አንድ ጊዜ በመገናኘት ስራውን ይገመግማ ያወያያል የትኩረት አቅጣጫ ያስቀምጣል
2. በትምህርት ቤት ደረጃ የወተመህ ምክር ቤት በሶስት ወር አንድ ጊዜ በመገናኘት ስራውን ይገመግማል ፣ ይወያያል የትኩረት ነጥቦችን ያስቀምጣል

3. በትምህርት ቤት ደረጃ የወተመ ምክር ቤት ስራ አስፈጻሚ በ15 ቀን አንድ ጊዜ በመገናኘት ስራውን ይገመግማል ፣ ይወያያል የትኩረት ነጥቦችን ያስቀምጣል
4. የወረዳ ተወማ ምክር ቤት ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በ15 ቀን አንድ ጊዜ በመገናኛት ስራውን የሰራል፣ ይገመግማል፣ የትኩረት አቅጣጫ ያስቀምጣል
5. የወረዳ ተወማ ምክር ቤት በሶስት ወር አንድ ጊዜ በመገናኘት ስራውን ያከናውናል፤ የገመግማል፣ ይወያያል የትኩረት አቅጣጫ ያስቀምጣል
6. የክፍለ ከተማ የተወማ ምክር ቤት ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በወር አንድ ጊዜ በመገናኘት ስራውን የገመግማል
7. የክፍለ ከተማ የተወማ ምክር ቤት በ 3 ወር አንድ ጊዜ በመገናኘት ስራውን ይመራል፣ የገመግማል፣ ይወያያል የትኩረት አቅጣጫ ያስቀምጣል
8. የከተማ ተወማ ምክር ቤት ስራ አስፈፃሚ በወር አንድ ጊዜ በመገናኘት ስራውን ይመራል፣ ይገመግማል፣ ይወያያል የትኩረት አቅጣጫ ያስቀምጣል
9. በትምህርት ቤት የወተመህ ምክር ቤት በዓመት ሶስት ጊዜ ከሁሉም ወላጆች ጋር ግንኙነት ማድረግ የትምህርቱን ስራ ይመራል
10. በከተማ፣ በክፍለ ከተማና በወረዳ ደረጃ በስራቸው ከሚገኙ የወተመህ ምክር ቤቶች ጋር በዓመት ሁለት ጊዜ የጋራ ግንኙነት በመፍጠር የትምህርቱን ስራ ይመራሉ፣ ይገመግማሉ፣ ይወያያሉ የትኩረት አቅጣጫዎችን ያስቀምጣሉ

## ክፍል አራት

### አንቀጽ 21. የመንግስት፣ የግልና መንግስታዊ ያልሆኑ ትምህርት ቤቶች አስተዳደርና የተቋሙ ባለቤቶች በወተመህ ኮሚቴ ተግባራት አፈፃፀም ላይ ያለባቸው ሀላፊነትና ተግባር

1. ኮሚቴው ለትምህርቱ ስራ ጠቃሚና አጋዥ መሆኑን በእምነት በመያዝ በነፃና ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ እንዲመረጥ ያደርጋል
2. የወተመህ ምክር ቤትና ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ተግባርና ሀላፊነቱን ባግባቡ እንዲወጣ አስፈላጊውን ሁሉ እገዛ ያደርጋል
3. በየደረጃ ያሉ የትምህርት አመራሮችና የትምህርት ቤት ልማታዊ ባለሀብቶች ለወተመህ ኮሚቴው የዕለት ተዕለት ሥራ ማከናወኛ ቢሮ ያመቻቻል

4. በግልና መንግስታዊ ባልሆኑ ትምህርት ቤቶች የትምህርት ቤቱ የክፍያ ለውጥ (በመቀነስም ሆነ በመጨመር) ከማድረጉ በፊት የትምህርት ዘመኑ ከመጠናቀቁ ከሶስት ወር አስቀድሞ ለትምህርት ቤት ለወተመህ ስራ አስፈፃሚ ስኮሚቴው ያሣውቃል፣ በህግና መመሪያው መሰረት በጋራ ይወስናል
5. ኮሚቴው በተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት ዙሪያ ዕቅድ ሲያዘጋጅ የሣተፋል
6. ስምምነት የተደረሰባቸውን ውሣኔዎችን በማክበር ያስፈፅማል

**አንቀጽ 22. የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም በትምህርት ዘርፉ የሚገኘው መምህር፣ የትምህርት አመራርና የትምህርት ተቋም ባለቤት የወተመህ ኮሚቴ ከምስረታ ጀምሮ በመመሪያው አተገባበር ላይ ለስራው የሚፈለገውንና የሚጠየቀውን መረጃና ሌላ ድጋፍ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

**አንቀጽ 23. የወተመህ ኮሚቴው የስራ ዘመን**

1. የኮሚቴው የስራ ዘመን ሶስት ዓመት ነው
2. እንደ አስፈላጊነቱ በጠቅላላ ጉባኤው ፍላጎት ለአንድ የምርጫ ዘመን ሊጨመር ይችላል
3. የአንድ ወተመህ ኮሚቴ ፍቃደኛ ከሆነና ጠቅላላ ጉባኤው ከመረጠው በድጋሚ ለአንድ ጊዜ ብቻ ሊመረጥ ይችላል
4. ወተመህ ኮሚቴው አባል በትምህርት ቤቱ ቢያንስ አንድ ልጅ የሚያስተምር ሲሆን ይገባል

**ክፍል አምስት**

የተማሪ ወላጅ ማህበር የበጀት ዓመት ከሐምሌ አንድ እስከ ሰኔ ሰላሳ ይሆናል፡፡

**የተማሪ ወላጅ ማህበር የገቢ ምንጭ**

1. ከተማሪ ወላጆች
2. ከትምህርት ቤት የውስጥ ገቢ
3. ከበጎ አድራጎት ድርጅቶች
4. ከሀገር በቀል ባለሀብቶችና ከበጎ አድራጊ ግለሰቦች
5. ከመንግስት ከሚመደብ በጀት

ለተማሪ ወላጅ ማህበር አደረጃጀቶች ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እስከ ትምህርት ቤት ባሉ የትምህርት ተቋማት በሁሉም ቦታ ቢሮ ያመቻቻል፡፡

## ክፍል ስድስት

### አንቀጽ 23. ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

1. **ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው አሠራሮች**

   1.1. ቀደም ሲል በየካቲት 2004 እና መጋቢት 2010 ዓ.ም የወጣው የወተመህ አደረጃጀትና አፈጻጸም መመሪያ በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

   1.2. የግል ትምህርት ተቋማት የትምህርት አገልግሎት አሰጣጥ እና ክፍያ ሥርዓት ሐምሌ 2007 የወጣ መመሪያ ክፍል አራት ከአንቀጽ 14፣ 15 እና 16 ስለ ወላጆች/አሳዳጊዎች እና ወላጅ ተማሪ መምህር ህብረት (የወተመህ) አደረጃጀት ከዚህ መመሪያ ጋር የማይፃረር መልኩ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

   1.3. ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ስለማንኛውም የትምህርት ዘርፍ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራሮች ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡

2. **መመሪያውን ስለማሻሻል**

   ይህ መመሪያ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በትምህርት ቢሮ እና በተማሪ ወላጅ ማህበር ሊሻሻል ይችላል፡፡

3. **መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ**

   ይህ መመሪያ ከዛሬ ህዳር 5 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ እና የተማሪ ወላጅ ማህበር

ህዳር 2012 ዓ.ም

አዲስ አበባ